# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 149 ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## መከላከያ ሕወሓት ያስረከባቸውን መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች የማንንዝ ሥራ መጀመሩን አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት ያስረከባቸውን መሣሪያዎች እና ተሽከርካሪዎችን የማንቀሳቀስ ሥራ መጀመሩን የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት አስታወቀ።

የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት እንደገለጸው፤ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት አመራሮች መካከል ደቡብ አፍሪካ እና ኬንያ ላይ በተደረሰው የሰላም ስምምነት መሠረት የተረከባቸው የተለያዩ ተሽከርካሪዎችና የጦር መሣሪያዎች ከቦታው መንቀሳቀስ ጀምረዋል።

ጥር 2 ቀን 2015 ዓ.ም ከመቀሌ 36 ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኘው አጉላ ካምፕ የአፍሪካ ሕብረት ወታደራዊ ታዛቢዎች በተገኙበት፣ ሕወሓት ያስረከባቸው መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ተተኳሾች ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ በኮንቮይ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን አስረድቷል።

በኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር የሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ ኮሎኔል ነጋ መንገሻ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ወታደራዊ ንብረቶቹን ተረክበን ከቦታው በማንሳት ወደ ተዘጋጀው ቦታ ጉዞ ጀምረናል ብለዋል።

በቀጠናው የተሰማራው ሰራዊት አመራር ሌተናል ኮሎኔል አለሜ ታደለ በበኩላቸው ተቋማችን የሰጠንን ትዕዛዝ በሚገባ ተገንዝበን ከሕወሓት አመራሮች ጋር በመነጋገር ተሽከርካሪዎችን እና መሣሪያዎችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መሠረት በመረከብ ለመከላከያ ሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ አስረክበናል ብለዋል።



## በክልሉ የመድኃኒት አስተዳደርን ለማዘመንና ሥርጭቱን ፍትሃዊ ለማድረግ እየተሠራ ነው

- የወባና የኤች.አይ.ቪ ሥርጭትን መግታት ላይ ትኩረት ተደርጓል

አመለወርቅ ከበደ

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል የመድኃኒት አስተዳደርን ለማዘመንና ሥርጭቱን ፍትሃዊ ለማድረግ እየተሠራ ነው ሲል የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር መንግሥቱ በቀለ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በክልሉ የመድኃኒት አስተዳደር ዘመናዊ አለመሆን ለመድኃኒቶች ብክነት እና ተደራሽነት አሉታዊ አስተዋፅኦ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በክልሉ የመድኃኒት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የዘንድሮው የበልግ ዝናብ ዘግይቶ ሊገባ እንደሚችል ተጠቆመ

ገመቹ ከድር

አዳማ፡- የ2015 ዓ.ም የበልግ ዝናብ በአንዳንድ አካባቢዎች ዘግይቶ ሊገባ እንደሚችል የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ኢንስቲትዩቱ ያለፈውን የበጋ ወራት አየር ጠባይ ሁኔታ ከኅብረተሰቡና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመገምገም የ2015 ዓ.ም የበልግ የአየር ጠባይን ይፋ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ በግምገማ መድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ ኢንስቲትዩቱ በኢትዮጵያ ያሉትን ወቅቶች መሠረት በማድረግ በበጋ ወቅት የተሰጠው ትንበያ እና በተጨባጭ በመሬት ላይ የታየው ክስተት መጣጣሙን ገምግሟል። ከዚህም በመነሳት የቀጣይ በልግ ዝናብ አጀማመር በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች ዘግይቶ ሊገባ እንደሚችል ጠቁሟል።

በመሆኑም በሚዘገይበት ጊዜ በተለይም በግብርና ሥራ ላይ ክፍተቶች እንዳይኖሩ አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስቧል።

በዘንድሮ በበጋው ወቅት በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች መደበኛ እና ከመደበኛ በታች የዝናብ መጠን እንደተስተዋለበት መተንበዩን የገለጹት ኃላፊው ይህም የመኸር ሰብልን ለመሰብሰብ በሰሜናዊ የአገሪቱ አጋማሽ

የዘንድሮው የበልግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



















# «የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸውን ዜጎች ለማስተማር የትምህርት ካሪኩለም መዘጋጀት አለበት»

- የፍቅር ኢትዮጵያ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ብሔራዊ ማህበር

# «የሕይወት ክህሎት ትምህርት ካሪኩለም ለማዘጋጀት የዳሰሳ ጥናት ሊጀመር ነው»

- ትምህርት ሚኒስቴር

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው ዜጎች የትምህርት ካሪኩለም መዘጋጀት አለበት ሲል የፍቅር ኢትዮጵያ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ብሔራዊ ማህበር አስታወቀ፡፡

የፍቅር ኢትዮጵያ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ብሔራዊ ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሸዋጌጥ ክብረት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸውን ዜጎች ለማስተማር የትምህርት ካሪኩለም በማዘጋጀት መንግሥት ችግሩ ያለባቸውን ዜጎች የመማር መብታቸውን ማስከበር አለበት ብለዋል፡፡

መንግሥት በአካቶ ትምህርት ዙሪያ የሠራቸው ሥራዎች ቢኖሩም በቂ የሚባሉ እንዳልሆኑ ወይዘሮ ሸዋጌጥ ተናግረዋል፡፡

በመዲናችን አዲስ አበባ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸውን ልጆች የሚማሩባቸው ጥቂት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች መኖራቸውን ገልጸው፤ ነገር ግን ይህ መልካም ጅማሮ በክልሎችም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ዜጎች የቀለም ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን የሙያ ማሠልጠኛዎች በመንግሥት ታቅደው ሊከፈቱ ይገባቸዋል ሲሉም አክለዋል፡፡



ወይዘሮ ሸዋጌጥ ክብረት



አቶ ዘውዱ ወልዴ

እንደ ወይዘሮ ሸዋጌጥ ገለፃ፤ በኢትዮጵያ ያለው የትምህርት ሥርዓት የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸውን ዜጎችን ያላካተተ ነው፡፡ የሌሎች አገራትን ተሞክሮ በመውሰድ የመማሪያ መጻሕፍት መዘጋጀት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም በብሔራዊ ፈተናዎች እና መደበኛ የመማሪያ ሰዓት የነዚህን ዜጎች ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሥርዓተ ትምህርት መቀረጽ አለበት ነው ያሉት፡፡

በኢትዮጵያ ወደ አራት ሚሊዮን ገደማ የሚሆኑ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች እንደሚኖሩ የተናገሩት ኃላፊዋ፤ ይህ ቁጥር ቀላል የሚባል እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡

ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግሥት ለዜጎቹ ተወካዮች የሚሆኑ ሰዎች እንዲኖሩ ዕድል ማመቻቸት እንዳለበት ገልጸው፤ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች የመሠልጠንና የመሥራት ዕድል ካገኙ አምራች ዜጎች መሆን እንደሚችሉም አክለዋል፡፡

በልጅነት ዕድሜያቸው የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት እንዳለባቸው ከታወቀ የንግግር ስልጠናዎች እና ሌሎች ድጋፎችን በመስጠት ያሉበትን ሁኔታ ማሻሻል እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ባለሙያ አቶ ዘውዱ ወልዴ እንደተናገሩት፤ የሕይወት ክህሎት ትምህርት ካሪኩለም ለማዘጋጀት የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ ታቅዷል፡፡

በአካቶ ትምህርት ውስጥ መግባት የማይችሉትን የሕይወት ክህሎት ትምህርት ለመስጠት የትምህርት ካሪኩለም ለማዘጋጀት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

መንግሥት አካቶ ትምህርት ከማስጀመሩ ጋር ተያይዞ ለዜጎቹ በሚመች መልኩ እንዲሆን የተለየ ካሪኩለም ባይኖርም መምህራን ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ እንዲከተሉ ለማድረግ የመምህራን መምሪያ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

አሁን ላይ ያለው የትምህርት ካሪኩለም ሁሉንም ዓይነት ተማሪዎች ያካተተ ስለመሆኑ ከመላው አገሪቱ ከተውጣጡ መምህራን ግምገማ እያደረጉ መሆኑን ተናግረዋል፡፡



# «አገር በኢኮኖሚ ጠንካራ ሆና እንድትቀጥል አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማጠናከር ያስፈልጋል»

- አቶ መላኩ አለበል

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- አገር በኢኮኖሚ ጠንካራ ሆና እንድትቀጥል እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎችን መፍጠር እንዲቻል አምራች ኢንዱስትሪውን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ አቶ መላኩ አለበል ተናግረዋል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ «ኢትዮጵያ ታምርት፤ ኦሮሚያ ታምርት ፤ ሸገር ታምርት» በሚል መሪ ሀሳብ አምራች ኢንዱስትሪው ላይ ያሉትን ማነቆዎች ለመፍታት እና አምራች ዘርፉን ለማነቃቃት በሸገር ከተማ አስተዳደር ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ አካሂዷል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል ውይይት መድረኩ ላይ ተገኝተው እንደተናገሩት፤ ድህነትን በማከፋፈል ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት አይቻልም፡፡ አገር በኢኮኖሚ ጠንካራ ሆና እንድትቀጥል እንደ አገር መካከለኛ ገቢ ያላቸው በርካታ የማህበረሰብ ክፍሎች መፈጠር አለባቸው፡፡

ሀብት ማፍራት የምንችለው አምራች ኢንዱስትሪው ላይ ያለውን ማነቆ በእንደዚህ ዓይነት መድረክ ተወያይተን መፍታት እና ለኢንዱስትሪው ምቹ የሆነ ቦታን ማመቻቸት ስንችል ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ታምርት አጀንዳ አምራች ኢንዱስትሪው ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ በየቤቱ እንዴት ማምረት ይችላል በሚል ላይ የሚያጠነጥን ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ ንቅናቄውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ካስጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ በሁሉም ክልሎች በተደረጉ ንቅናቄዎች ከፍተኛ ውጤቶች ተመዝግበውበታል ብለዋል፡፡

በእኛ በኩል ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘላቂ መፍትሄ ሊሰጥ የሚችል ፖሊሲ አዘጋጅተን ጨርሰናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህ ፖሊሲ በሚቀጥለው አስር አመት አምራች ኢንዱስትሪው ለኢትዮጵያ የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ የሚያደርግ ነው ብለዋል፡፡

ሚኒስትሩ አክለውም ባለሀብቶች በማበረታቻነት የተሰጣችሁን መሬት በአግባቡ በማልማት ለአርሶአደሩ እና ለከተማው ነዋሪ የሥራ ዕድል የመፍጠር ኃላፊነት አለባችሁ ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል ፡፡

የሸገር ከተማ ከንቲባ አቶ ተሾመ አዱኛ እንደገለጹት፤ በአገርም ሆነ በከተማ ደረጃ የአምራች ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ተጽእኖ አለው፡፡ የአምራች ዘርፉን ማጠናከር ለባለሀብቱ ብቻ ሳይሆን ለአገርም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ብለዋል፡፡

በሸገር ከተማ አራት ሺህ 144 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚገኙ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥም ሁለት ሺህ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ገብተዋል፤ 397 ፕሮጀክቶች ደግሞ የግንባታ ሥራቸውን ያጠናቀቁ ናቸው፡፡ የተቀሩት ፕሮጀክቶች መሬት ወስደው ወደ ሥራ ያልተገባባቸው እንደሆኑም ተጠቁሟል፡፡

# በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረው ችግር በሰላማዊ መንገድና በቤተ ክርስቲያኒቱ አሠራር እንዲፈታ ሁሉም ኃላፊነቱን ይወጣ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከሰሞኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል የተፈጠረው መለያየት በሰላማዊ መንገድ በውይይትና በቤተ ክርስቲያኒቱ አሠራር መሠረት እንዲፈታ ሁሉም አካላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ትናንት ባወጣው መግለጫ፤ ከሰሞኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል የተፈጠረው መለያየት ሰላማዊ በሆነ መንገድ፣ በውስጣዊ አሠራር እንዲፈታ መንግሥት ጽኑ ፍላጎት እንዳለው ገልጿል።

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ አገራዊ ተቋማት አንድነታቸውንና ጥንካሬያቸውን ጠብቀው እንዲዘልቁ ከዚህ በፊትም ሆነ ችግሮች በተፈጠሩ ጊዜ ሁሉ መንግሥት የሚጠበቅበትን ሲወጣ ቆይቷል። ይሄንን ጥረቱን አሁንም አጠናክሮ ይቀጥላል።

የተቋማቱን አንድነት የሚፈታተኑ ችግሮች ከውስጥ ሲነሡ በውይይትና በውስጣዊ አሠራር እንዲፈቱ ድጋፍ ሲያደርግ ነበር። በተጨባጭ ውጤት አምጥቷል ሲል አገልግሎቱ ጠቁሟል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል የተፈጠረው መለያየት በሰላማዊ መንገድ በውይይትና በቤተ ክርስቲያኒቱ አሠራር መሠረት እንዲፈታ የአገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ሁለቱን ወገኖች በማቀራረብ ችግሩን በሰከነ መንገድ እንዲፈታ ማድረግ አለባቸው ሲል መንግሥት አስታውቋል።

አማኞች ችግሩን ከማወሳሰብና ለሌሎች አካላት መጠቀሚያ ከመሆን በመታቀብ ገንቢ ሚና ሊጫወቱ እንደሚገባ በመግለጫው ተመላክቷል።

የጸጥታ አካላት የየአካባቢውን ሕዝብና የእምነት ተቋማት ሰላምና ጸጥታ ማስከበር ግዴታቸው መሆኑን የጠቆመው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ፤ ግጭት የሚያባብሱ አካላትንም ሥርዓት ማስያዝ እንዳለባቸው አሳስቧል።

አገልግሎቱ እንደገለጸው፤ የሚዲያ አካላት ችግሩን የሚያባብሱ ነገሮችን ከማቅረብ መቆጠብ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም መላው ሕዝብ ለችግሩ መፈታት የሚጠበቅበትን ማድረግ አለበት።

በሌላ በኩል እምነትና ብሔርን ተገን አድርገው ግጭት ለመፍጠር የሚያስቡ፣ አገር ለማፍረስ በተለያዩ መንገዶች ሞክረው ያልተሳካላቸው ኃይሎች፣ ችግሩ እንዲባባስና እንዳይፈታ ለማድረግ እየሠሩ መሆኑ ተደርሶበታል ሲል አገልግሎቱ አስታውቋል።

ችግሩ እንዲባባስና እንዳይፈታ ለማድረግ የሚጥሩ አካላትን መንግሥት ፈጽሞ እንደማይታገስ በመግለጫው ተመላክቷል።

ችግሩን ለማባባስና በሕዝቦች መካከል ግጭት ለመፍጠር፣ ብሎም አገርን ወደፈተና ለማስገባት በሚጥሩ አካላት ላይ መንግሥት ሕግ የማስከበር ሥራውን እንደሚሠራ አሳውቋል።

ዜና

# ጊኒ ዎርምን ለማጥፋት የሚደረገው የቅኝት ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል



**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- የጊኒ ዎርም በሽታን ለማጥፋት በቤትና በዱር እንስሳት ላይ የሚደረገው የቅኝት ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የበሽታው ምልክት በጋምቤላ ክልል ሁለት ወረዳዎች ጎግና አበቦ በሰዎችና በዝንጀሮዎች ላይ መታየቱም ተገልጿል።

የኢንስቲትዩቱ የበሽታና ሌሎች የጤና ኩነቶች ክትትል ዳይሬክተር አቶ መስፍን ወሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችንና አጋር ድርጅቶች ባሳተፈ መልኩ በአገር ደረጃ የጊኒ ዎርም በሽታን ለማጥፋት በተጠናከረ ሁኔታ እየተሠራ ነው።

የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን በማሻሻል፤ በሰዎች እንዲሁም በቤትና በዱር እንስሳት ላይ ተከታታይነት ያለው የቅኝት ምላሽ በመስጠት በሽታውን መከላከልና ማጥፋት እንደሚቻልም ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

በሽታውን ለመከላከልና ለማጥፋት ውሃ ያቆሩ ጉድጓዶችን በኬሚካል የማከም ሥራ በስፋት እየተሠራ መሆኑን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፣ ሆኖም ግን ጥልቀት ያላቸውና ከሰዎች ርቀው የሚገኙ የውሃ ጉድጓዶችን በሚፈለገው ልክ ማከም አስቸጋሪ መሆኑን አስረድተዋል።

በቤት እንስሳት ላይ ያለውን የበሽታው ሁኔታ ለመለየት ዓለምአቀፍ ረጂ ድርጅቶች ጋር በመሆን ሰፊ ጥናትና ቅኝት እየተሠራ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ነገር ግን በዱር እንስሳት ላይ የሚደረገው ቅኝት እንስሳቱ በአደን ተገድለው ወይም በሌሎች ምክንያት ሞተው ካልተገኙ የቅኝት ሥራውን አዳጋች ያደርገዋል ነው ያሉት።

በአገሪቱ ቀድመው በሽታውን በመከላከል ለማጥፋት በመሥራት ላይ ያሉት ሊጠናከሩ ይገባል ያሉት አቶ መስፍን፣ በቀጣይ የበሽታው ምልክት በታየባቸው አካባቢዎች የቤትና የዱር እንስሳት ላይ የሚደረገው የቅኝት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በሽታውን ለማጥፋት በሚደረገው ጥረት የትብብር እና የቅንጅት ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል አስፈላጊ እንደሆነ አቶ መስፍን ገልፀዋል።

በሽታውን የማጠፋት ሥራው ውጤታማ እንዲሆንም ማህበረሰቡን የማስገንዘብና የማንቃት ሥራው ከተለመደው ባህላዊ አሠራር በመውጣት በዘመነ መልኩ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል።

በተጨማሪም የበሽታውን የመከሰት ሁኔታ ማጥበብ ሥራዎችን በስፋት ማካሄድ፣ ቴክኖሎጂን መጠቀም እና በሽታውን በማጥፋት ጥሩ ተሞክሮ ካላቸው አገራት ልምድ መቅሰም ለቀጣይ እንደቤት ሥራ በመውሰድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉም በኃላፊነት ሊሠሩ ከሚገባቸው ሥራዎች መካከል መሆኑን አመላክተዋል።

# ‹‹በጦርነት የደረሰውን ጉዳት መልሶ ለመገንባት የድርሻችንን እንወጣለን‹›

\- ዳያስፖራዎች

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያን ለመደገፍ ሲያደርጉት የነበረውን እንቅስቃሴ አጠናክረው እንደሚቀጥሉና በጦርነት የደረሰውን ጉዳት መልሶ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የድርሻቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆናቸውን ዳያስፖራዎች ገለጹ።

ከካናዳ ኦቶዋ የመጡት አቶ ሰማነህ ታምራት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት ኢትዮጵያ የደረሰባትን ጫና ለማቃለልና ሉዓላዊነቷን ለማስከበር በተለያዩ ክፍለ ዓለማት የሚገኙ ዳያስፖራዎች ከፍተኛ ተጋድሎ ሲያደርጉ ቆይተዋል። በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የሰላም ስምምነት ተደርሶ ጦርነት መቆሙም አብዛኛውን ዳያስፖራ አስደስቷል ብለዋል።

በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መልሶ ለመገንባትና ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም መረባረብ ይገባል ያሉት አቶ ሰማነህ፤ ዳያስፖራውም የመልሶ ግንባታ ሥራዎችን በመደገፍና በተለያዩ መስኮች መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲያገግም የድርሻውን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለበት ጠቁመዋል።

ሠላም ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ ለዘላቂነቱ ሁላችንም መተባበር አለብን ያሉት አቶ ሰማነህ፤ እንደ አገር ዘላቂ ሰላም ሰፍኖ ዜጎች በሠላም ወጥተው እንዲገቡ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከማንነትና ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ግጭቶችን መፍታት ይገባል ብለዋል።

ከአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ የመጡት አቶ ዳንኤል እያሱ በበኩላቸው፤ ሠላም እንደ አገር የምናተርፍበት በመሆኑ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው ስምምነት አስደሳች መሆኑን ገልጸዋል።

የተደረሰው ስምምነትና እየታየ ያለው ሰላም ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንፈልጋለን ያሉት አቶ ዳንኤል፤ በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች መልሶ ለማቋቋምና ወደ ቀደመ ሕይወታቸው ለመመለስ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት መተባበር ይጠቃል።

እኛም ቀደም ሲል ስናደርገው የነበረውን ድጋፍ በመልሶ ግንባታው ላይም የድርሻችንን ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁ ነን ብለዋል።

ከአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ የመጡት ወ/ሮ ልደት ሙለታ እንዳሉት፤ ዳያስፖራው ኢትዮጵያን በመወከል በዓለም መድረክ ላይ በመከራከር፣ የታላቁን የህዳሴ ግድብ በመደገፍና በሌሎችም መስኮች የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱን ገልጸዋል።

በቀጣይም ዳያስፖራዎችን በማስተባበር በኢንቨስትመንት፣ በሌሎች የልማት ሥራዎች ለመሳተፍና ኢትዮጵያን ወደ ከፍታ ሊወስዱ የሚችሉ ተግባራትን ለማከናወን መዘጋጀታቸውን አስረድተዋል።

ዳያስፖራው ተሳትፎ የሚያደርገው ተመችቶት ሳይሆን ቅድሚያ ለአገሬ በሚል ስሜት ነው የሚሉት ወ/ሮ ልደት፤ ሁሉም የሚያምረው በአገር ስለሆነ የተጀመሩ መልካም አገራዊ እንቅስቃሴዎችን ለመደገፍና የተደረሰው የሰላም ስምምነት ከዳር እንዲደርስ ሁላችንም በጋራ እንቁም የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

ባለፈው ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም በተለያዩ ዘርፎች የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱና ከ25 አገራት ለተውጣጡ 52 የዳያስፖራ አደረጃጀቶች እውቅና መሰጠቱ ይታወሳል።



አቶ ሰማነህ ታምራት



ዳንኤል እያሱ




ልደት ሙስታ

# «በመንግሥት የተበረከተው እውቅናና ሽልማት ዳያስፖራው የበለጠ እንዲንሠራ አደራ የጣለ ነው»

\- አቶ አለባቸው ደሳለኝ

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በቅርቡ በውጭ ሆነው ለአገራቸው ዘብ በመቆም የበኩላቸውን ጥረት ላደረጉ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ‹‹ኢትዮጵያ ታመሰግናለች›› የሚል መርሃ ግብር በማዘጋጀት የሰጠው ሽልማትና እውቅና ለእስካሁኑ ሥራ የተበረከተ ብቻ ሳይሆን በቀጣይም የበለጠ እንዲሠራ አደራ የጣለ መሆኑን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት ዘርፍ የእውቅና ፕሮግራም ኃላፊ አቶ አለባቸው ደሳለኝ አስታወቁ፡፡

አቶ አለባቸው ደሳለኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ እስከ ዛሬ ባለው ተሞክሮ ዳያስፖራው የቱንም ያህል ለአገሩ አምባሳደር ሆኖ ቢሟገትና ቢለፋ በመንግሥት ደረጃ ምስጋናና እውቅና መስጠት የተለመደ አይደለም፡፡

በቅርቡ መንግሥት በተለየ ሁኔታ እውቅና መስጠቱ በዳያስፖራው ውስጥ ከፍተኛ የሞራል መነቃቃትን ይፈጥራል፤ በቀጣይም ዳያስፖራው በላቀ መንፈስ ለአገሩ ዘብ እንዲቆም ጉልበት ይሆነዋል፡፡ ይሁንና የሰጠው ሽልማት ምስጋና እና እውቅና ብቻ ሳይሆን የበለጠ ለመሥራት የተሰጠ አደራ ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት ‹‹እናመሰግናለን›› ብሎ በአገር አቀፍ ደረጃ ሽልማት ሲሰጥ መልዕክቱ የሁሉም ኢትዮጵያዊ መሆኑን እረዳለሁ ያሉት አቶ አለባቸው፤ በርካታ ዳያስፖራዎች አገራዊ ስሜታቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚያደርግ የእውቅና መርሃግብር በመደረጉ ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ሽልማቱ በስደት አገር ሆነን ለምንሰራው ሥራ ለካስ ተመልካች አለ፤ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚያሳስበው አካል አለ፤ ብለን እንድናስብ አድርጎናል። ለእኔ እውቅናው ይህንን የሕዝብ ኃላፊነት ይዘን እንድንመለስ ማሳሰቢያም ጭምር ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከሁሉ በላይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ያለበትን የጋራ ኃላፊነት፤ ብሔራዊ ግዴታውን የሚወጣበት መልዕክት የተላለፈበት መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይም ደግሞ ወቅቱን በጠበቀ መንገድ እውቅና መስጠቱ በመንግሥትና በዳያስፖራው መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር የሚያግዝ መሆኑን አቶ አለባቸው ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት በውጭ አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር ያለውን መልካም ግንኙነት ለማጠናከር የወሰዳቸው እርምጃዎች የዳያስፖራ የተግባር ምክር ቤት በአድናቆት ነው የተመለከተው ብለዋል፡፡


በመንግሥት እውቅናው የተሰጣቸው አካላት በአብዛኛው በቀደሙት ዓመታት በኤምባሲዎችና በቆንስላዎች አደረጃጀት ተፈጥሮላቸው የሚታወቁ የዳያስፖራ ማህበራትና ግለሰቦችን ብቻ ያካተተ መሆኑን ተናግረው፤ ይህም በርካታ ሥራዎችን ያከናወኑና ለአገራቸው ሲሉ ዋጋ የከፈሉ ሌሎች ዳያስፖራዎች ላይ ቅሬታ ሊፈጥር ስለሚችል ወደፊት ሁሉንም ያካተተ እንዲሆን በጥንቃቄ መስራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

በቀጣይም የዳያስፖራ ኤጀንሲ ለአገራቸው አምባሳደር ሆነው ዋጋ እየከፈሉ ከሚገኙ ዳያስፖራዎች ጋር ያለውን ግንኙነት የበለጠ ማጠናከር እንዳለበት መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በተለይ ዳያስፖራውን በሚገባ በማወቅና ተግባብቶ በመሥራት አኳያ ውስንነቶች እንደነበሩ ጠቁመው፤ ኤጀንሲው ከኤምባሲዎችና ቆንስላዎች ጋር በመናበብ በመንግሥት አደረጃጀት ውስጥ የሌሉትን ሁሉ በማካተትና በማሳተፍ የበለጠ ለአገራቸው እንዲሠሩ መደገፍ እንዳለበት አቶ አለባቸው ተናግረዋል፡፡

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ምክር ቤት በአሁኑ ወቅት የአገር ገፅታን በመገንባት፣ ዳያስፖራው ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ ቱሪዝምና ኢንቨስትመንት እንዲሳተፍ ቅስቀሳ በማካሄድና መልካም ትውልድ በመቅረፅ ረገድ ሰፊ ሥራዎችን እያከናወነ ነው፡፡

በተለይም አብዛኛው ዳያስፖራው አገሩንና ታሪኩን በሚገባ እንዲያውቅ ለማድረግ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ 127ኛው የዓድዋ በዓል በዓለም አቀፍ ደረጃ በደመቀ ሁኔታ ለማክበር የዓድዋ ዘካሪያን ማህበር አቋቁሞ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ነው ብለዋል፡፡





አቶ ደረጄ ተግይበሉ

# ከስደት የተመለሱ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም በትኩረት እየተሠራ ነው

- ከሳውዲ አረቢያ ብቻ 105 ሺህ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ቤት ተመልሰዋል

**በሪሁ አረጋ**

አዲስ አበባ፡- ከስደት የተመለሱ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም በትኩረት እየተሠራ እንደሆነ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ እስከ አሁንም 105 ሺህ ኢትዮጵያውያን ከሳውዲ ወደ አገራቸው መመለሳቸውም ተገልጿል፡፡

በሚኒስቴሩ የሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ክትትልና ድጋፍ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ደረጀ ተግይበሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ ከሚያዝያ 2014 ዓ.ም ጀምሮ 105 ሺህ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ከሳውዲ ወደ አገራቸው ተመልሰዋል፡፡ ሰደተኞቹን መልሶ ለማቋቋም በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡

ሳውዲ ዓረቢያን ጨምሮ ከተለያዩ የውጭ አገራት ወደ አገራቸው የሚመለሱ ዜጎች አቀባበል ከተደረገላቸው በኋላ የጤና ችግር ያለባቸው በሆስፒታል ህክምና እንደሚደረግላቸው እና ተላላፊ በሽታ ያላቸው ሰዎች ካሉ ደግሞ በተለየ ቦታ እንዲቆዩ ይደረጋል ሲሉ አቶ ደረጄ ገልፀዋል፡፡

መንግሥት ከስደት ተመላሾቹ በአገራቸው ሰርተው እንዲለወጡ፣ ሕይወታቸውን በተገቢው መንገድ መምራት እንዲችሉ የተለያዩ ስልጠናዎችና ድጋፎች እስከ አራት ወር ድረስ ይሰጣቸዋል ያሉት አቶ ደረጄ፤ ሥልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደሚፈልጉት ሙያ እንዲሰማሩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል ብለዋል፡፡

ሥልጠናው ከሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም ከክልል ቢሮዎች ጋር በመሆን ለስደት ተመላሾች እንደሚሰጥ የገለጹት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ በአገሪቱ ባሉት የሥራ ዕድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑም አስፈላጊው ሁሉ እየተመቻቸላቸው እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

አብዛኛው ከስደት ተመላሾች ከክልሎች የመጡ በመሆናቸው ከክልል መንግሥታት ጋር በመሆን የማደራጀት፣ የማሰልጠንና ወደ ሥራ የማስገባት እንቅስቃሴው ጥሩ ደረጃ ላይ መሆኑንም አክለው ገልጸዋል፡፡

የፌዴራል መንግሥትም ከስደት ተመላሾቹ መነሻ ካፒታል በመያዝ ወደ ሥራ እንዲገቡ እየሠራ መሆኑን ያብራሩት አቶ ደረጀ፣ መንግሥት ስደተኞችን መልሶ ለማቋቋም ከመደበው በጀት በተጨማሪ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ የማፈላለግ ሥራ እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

አብዛኞቹ ከስደት ተመላሾች መታወቂያ ስለሌላቸው ከኅብረተሰቡ ጋር ከተቀላቀሉ በኋላ መልሶ የማቋቋም ሥራ በሚሠራብት ጊዜ መለየት እንደሚያስቸግር እንዲሁም ለመደራጀት ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ መሆን መልሶ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት ሥራዎችን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እየፈጠረብን ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ከፍተኛ የጤና እክል የገጠማቸው ስደተኞች መንግሥት ህክምና ካደረገላቸው በኋላ የትራንፖርት ገንዘብ በመስጠት ወደ መጡበት እንዲመለሱ እየተደረገ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

# በኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ማኅበራቱ ሊጠናከሩ ይገባል

**መክሲት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በኮንስትራክሽን ዘርፍ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታትና ሙያውን ለማሳደግ መንግሥት የሙያ ማኅበራትን መደገፍ እና አብሮ መሥራት አለበት ሲል የኢትዮጵያ ቅየሳ ማህበር አሳሰበ፡፡

የኢትዮጵያ ቅየሳ ማህበር ፕሬዚዳንትና በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ረዳት ፕሮፌሰር ጥላሁን ኡርዶኖ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት በኮንስትራክሽን ዘርፍ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታትና ከሙያው የሚገኘውን አገልግሎት ለማሳደግ የሙያ ማኅበራትን መደገፍ እና አብሮ መሥራት አለበት፡፡

ተዛማጅ የሆኑ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ከሚመለከታቸው ማኅበራት ጋር በጋራ ቢሠሩ አገሪቷ ላይ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ያስችላል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ አሁን ላይ ባለው ሁኔታ በጋራ የመሥራቱ ነገር በሚፈለገው ልክ እንዳልሆነ ተናግረው፤ የሙያ ማኅበራትም ሙያዊ ተጽዕኖ መፍጠር እንዳልቻሉ አስረድተዋል፡፡

ማኅበራት ውስጥ ከፍተኛ የባለሙያዎች ስብስብ ያለ በመሆኑ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ማህበራትን ማገዝ፤ ማጠናከርና አብሮ ለመሥራት ተነሳሽነት ማሳየት አለበት ሲሉም አስተያየታቸውን አክለዋል፡፡

መንግሥት ከኮንስትራክሽን ማህበራት ጋር ቢሠራ በዘርፉ የሚስተዋሉትን በርካታ ችግሮች እንደሚቀርፍ ያመላከቱት ረዳት ፕሮፌሰር ጥላሁን፤ ለአብነትም በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ከሚስተዋሉ ተመሳሳይ ዓይነት የሕንፃ ጥበቦች በመውጣት ከሙያ ማኅበራት ጋር በመሆን አዳዲስ የሕንፃ ጥበባትን መፍጠር እንደሚቻል አንስተዋል፡፡

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ጥላሁን ገለጻ፤ የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማኅበር ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ጋር ቢሠሩ፤ የኢትዮጵያ የቅየሳ ባለሙያዎች ማኅበር ከኢትዮጵያ ካርታ ሥራዎች ወይም የስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ ጋር በቅንጅት ቢሠሩ ተጨባጭ ለውጦችን ማምጣት ይቻላል፡፡



ረዳት ፕሮፌሰር ጥላሁን ኡርዶኖ



አቶ ፈንታ ደጀኔ

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፈንታ ደጀኔ በበኩላቸው በሰጡት ምላሽ፤ መንግሥት በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን እና ማኅበራትን ለማብቃት ሥራዎች እየተሠሩ እንዳሉ ተናግረዋል፡፡

መንግሥት የኮንስትራክሽን ዘርፉን ለማዘመን በዘርፉ የሚገኙ ተዋንያንን በመደገፍ እና በማብቃት የተሻለ ሥራዎችን ለመሥራት መልካም ጅማሮዎች እንዳሉ ያብራሩ ሲሆን፣ ከዚህ በፊትም የተለያዩ ሰነዶች ቀርበው በዘርፉ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ሊያግዙ በሚችሉበት መልኩ እንዲተገበሩ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ እንዳሉ ተናግረዋል፡፡

# በክልሉ የመድኃኒት አስተዳደርን ለማዘመንና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የዘመነ የመድኃኒት አስተዳደር ሥርዓት አለመገንባቱ የሚያስከትላቸውን ችግሮች በመገንዘብ 200 በሚሆኑ የጤና ተቋማት የአሠራር ሥርዓታቸው በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ተደርጓል። ይህም የመድኃኒት ብክለትን ከሁለት በመቶ በታች እንዲሆን አድርጓል።

የአቅርቦት ችግርን በመቅረፍ በኩል የክልሉ መንግሥት 411 ሚሊዮን ብር በመመደብ የተለያዩ መድኃኒቶችን መግዛቱን ያሳወቁት ኃላፊው፤ በተጨማሪም የመድኃኒት እጥረትን ለመቅረፍ 73 የኅብረተሰብ መድኃኒት መደብሮችን መጨመር ተችሏል ሲሉ ገልፀዋል።

ዶክተር መንግሥቱ እንደገለፁት፤ ባለፉት ስድስት ወራት አምስት ሺህ 900 የህክምና ተቋማት ላይ ቁጥጥር ተደርጎ ከዚህ ውስጥ ደረጃቸውን ጠብቀው አገልግሎት እየሰጡ ላልነበሩ ከአንድ ሺህ 700 በላይ ለሚሆኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። 373 የሚሆኑት ሙሉ በሙሉ ተዘግተዋል።

በቀጣይ በመድኃኒት፣ በህክምና መሣሪያዎች ያለውን የአቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ እና ያሉትን ተቋማት በመሠረተ ልማት ለማሟላት ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ በመግለጽ፤ በግጭት ምክንያት የተጎዱ የህክምና ተቋማትን መልሶ መገንባት ሌላኛው የትኩረት አቅጣጫ እንደሆነ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ከተላላፊ በሽታዎች አንፃር የወባና ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ሥርጭትን ለመግታት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት የወባ ሥርጭት መጨመሩን አንስተው፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን የደም ምርመራ ተደርጎ 300 ሺህ ሰዎች የወባ በሽታ ተገኝቶባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ስርጭቱን ለመቀነስ የተለያዩ ሥራዎችን ሠርተናል ያሉት ኃላፊው፤ በዚህም የኬሚካል ርጭት እና ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን አጎበር መሠራጨቱን ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ አሁን ላይ ከ122 ሺህ በላይ ሰዎች የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድኃኒት እየወሰዱ እንደሚገኙ ዶክተር መንግሥቱ ገልፀዋል።

ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ውስጥ አምሥት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ የደም ግፊት ምርመራ ማድረግ መቻሉን አክለው የገለጹት ዶክተር መንግሥቱ፤ ሆኖም የኅብረተሰብ ክፍሉ የደም ግፊት ምርመራ የማድረግ እና በተገቢው ሁኔታ ክትትል የማድረግ ባህሉ ደካማ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡ ሰዎች ስለጤናቸው እንዲያውቁ በዘመቻ መልክ እየተሠራ መሆኑንም የጤና ቢሮ ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

# የዘንድሮው የበልግ ዝናብ ዘግይቶ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አካባቢዎች ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮ እንደነበር ገልጸዋል።

አቶ ፈጠነ እንደገለጹት፤ ቀጣዩ በልግ በአሁኑ ሰዓት በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት መደበኛ ሁኔታ (ENSO-Neutral)እና በሰሜናዊ ሕንድ ውቅያኖስ መደበኛ የባህር ወለል ሙቀት (Neutral IOD) በመሆኑ ምክንያት ሊዘገይ ይችላል። ይህንን ክስተት ምክንያት በማድረግ የ2015 ዓ.ም በልግ ዝናብ አጀማመር ዘግይቶ ሊገባ ይችላል። አወጣጡ ግን መደበኛ ጊዜውን ጠብቆ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በበልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡብና ደቡብ ምሥራቅ አገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ላይ መደበኛ ዝናብ ይኖራቸዋል። የምዕራብ አጋማሽ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ፤ ሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛና ምሥራቅ፣ የደቡብ ደጋማ የአገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ መደበኛ የሆነ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ትንበያው አመላክቷል። በአብዛኛው የአገሪቱ አካባቢዎች የየቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን ከመደበኛው አንጻራዊ መጨመር እንደሚኖረውም ይጠበቃል።

የሙቀት መጠን መጨመር የተፋሰስ አካላት ላይ ተጽዕኖ በማሳደር በኃይል አቅርቦት፤ በመጠጥ ውሃ፣ በመስኖ እርሻ ዘርፍ ፣ የእንስሳት መኖ እጥረት ሊያስከትል ስለሚችል ኅብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

በተለይም ባለፈው ወቅት በድርቅ ተፅዕኖ ስር የነበሩ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ የተሰጠውን ትንበያ ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር የኢንስቲትዩቱን ምክረ ሃሳብ ተግባራዊ እንዲያደርግ ዳይሬክተሩ መክረዋል።

በተያያዘ ዜና ጎርፍ ሊያስከትሉ የሚችሉና መሰል መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ፈጠነ፣ ከአንድ ራዳር ወደ አራት ራዳር ማሳደግ ተችሏል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሜትሮሎጂ ትንበያ እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር አሳምነው በምክክር መድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ የ2015 ዓ.ም የበልግ አየር ሁኔታ መደበኛ እና ከመደበኛ በታች የዝናብ መጠን ሊኖረው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች አመላክተዋል ብለዋል።

በዚህ ወቅት ከመደበኛው በላይ ሙቀት ሊኖር እንደምችል የገለጹት ዶክተር አሳምነው፤ ይህ ክስተት ከአጀማመሩ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል አያይዘው ገልፀዋል።

የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዶክተር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ በምክክር መድረኩ ላይ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቀርቡ መረጃዎች ዜጎች እና መንግሥት ስለአየር ጸባይ ሁኔታ አስቀድመው መረጃ እንዲኖራቸውና ለመፍትሄው እንዲዘጋጁ የሚያደርግ ነው።

ሁሉም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቀረበው መረጃ መሠረት ዜጎችን ከአደጋ ለመከላከል ወደ ፊት በሚሠሩ ሥራዎች ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱም ሚኒስትሩ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የለውጡ ጉዞ ትዕግስትን፣ ብስለትንና ጽናትን ይጠይቃል!

ለውጥ እና ለውጥ የሚሸከማቸው አስተሳሰቦች ይዘዋቸው ከሚመጡት ከፍያሉ ተስፋዎች አንጻር ብዙዎች በለውጥ እና በለውጥ ኃይሉ ተስፋ ለማድረግ አይቸገሩም። ከዚህ የተነሳም ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ የለውጥ ኃይል ሆነው የሚሰለፉ ቁጥራቸው የትየለሌ ነው፤ የቁጥራቸውንም ያህል መነቃቃታቸው ረጅም መንገድ መጓዝ የሚያስችል አቅም መስሎ የሚታይ ነው።

በተለይም ለውጡ በብዙ ገፌ ምክንያቶች ወይም ስብራቶች ተጸንሶና ሕይወት ዘርቶ የተወለደ ከሆነ፤ የለውጡ ባለቤት በሆነው በሕዝቡ ዘንድ የሚጣልበት ተስፋ ትናንቶችንና በትናንቶች ውስጥ ተወልደው ያደጉ፤ የገነገኑ ችግሮችን ምንነት ታሳቢ ያደረገ ባለመሆኑ በራሱ ለለውጡ ዋነኛ ተግዳሮት መሆኑ የማይቀር ነው። ይህ ደግሞ ለውጥ በተካሄደባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ጎልቶ የተስተዋለና አሁንም የሚስተዋል ክስተት ነው።

ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ የለውጥ ኃይል ሆኖ የሚሰለፈው ሕዝብ፤ በመሠረታዊነት ትኩረት አድርጎ የሚጓዘው የቀደመውን / አሮጌውን የፖለቲካ ሥርዓት ማስወገድ ላይ ነው። ይህ በራሱ ሥርዓቱን በማስወገድ ሂደት ውስጥ የተሻለ አቅም እንዲኖረው የሚያስችለው ቢሆንም፤ ሥርዓቱ የተፈጠረውን ችግር በአግባቡ ተረድቶ ችግሩን በማከም ሂደት ውስጥ ሊያጋጥም የሚችለውን ፈተናና በፈተና ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ጽናት እንዲያስተውል ዕድል አይሰጠውም።

ከዚህ የተነሳም አሮጌው ሥርዓት በተወገደ ማግስት ለለውጡ ገፌ የሆኑ ምክንያቶች /ስብራቶች/ ሁሉ ወዲያው ታሽተውና ተጠግነው ፈውስ እንዲያገኙ የመፈለግ አዝማሚያዎች ጎልተው ይታያሉ፤ ይህ ፍላጎት ሳይሳካ ቀናት እየተቆጠሩ በሄዱ ቁጥርም በለውጡ ተስፋ ማጣት፤ ለፈተናዎች መንበርከክና እጅ መስጠት ጎልቶ መታየት ይጀምራል። ይህ ደግሞ ለለውጡ ኃይል ተጨማሪ ፈተና ከመሆኑም በላይ ለውጡ በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይቀጥል ተግዳሮት ይሆናል።

በአገራችን ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ እየሆነ ያለውም ብዙም ከዚህ የተለየ አይደለም። ለውጡ በብዙ ገፌ ምክንያቶች /ስብራቶች/ ሕይወት ዘርቶ አገራዊ የተስፋ ብስራት ይዞ መምጣቱን ተከትሎ መላው ሕዝብ የለውጡ ባለቤት ስለመሆኑ በተለያዩ መንገዶች አሳይቷል። ለውጡን ለማራመድ ያሳየው መነቃቃት በአጭር ጊዜ ረጅም ርቀት መጓዝ የሚያስችለው አቅም ሊሆን እንደሚችልም ያሳየ ነበር።

ትናንት ተወልደው ያደጉ፤ የገነገኑት አገራዊ ችግሮቻችን /ስብራቶቻችን የለውጡ ባለቤት የሆነው ሕዝባችን እንዳሰበውና እንደጠበቀው በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ታሽተውና ተጠግነው ፈውስን መጎናጸፍ አለመቻላቸው፤ ከዚህም በላይ ስብራቶቹ በማደንዘዣ ታሽተው የታሸጉበት ፋሻ ሲፈታ እየተፈጠረ ያለው እውነተኛው የስብራት ስሜት የለውጥ ተስፋውን እየተፈታተነው ይገኛል።

ይህ በመሠረታዊነት የለውጡ ባለቤት የሆነው ሕዝቡ አሮጌውን ሥርዓት ከመለወጥ ባለፈ ፤ ለውጡን በማስቀጠል የለውጡን ተስፋዎች/ ትሩፋቶች ባለቤት ለመሆን በቀጣይነት የሚያስፈልገውን የትግል ዝግጁነት በአግባቡ ካለመረዳት፤ ለውጡን የአንድ ጊዜ ትግል አድርጎ ከመውሰድ የሚመነጭ የአረዳድ ችግር ነው።

በርግጥ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሄ እያስቀመጡ ከመጓዝ ይልቅ፤ ችግሮችን እያድበሰበሱና እየሸፋፈኑ የማለፍ ልምምድ በዳበረበትና ይህን እንደ አንድ የችግር አፈታት ባህል ተደርጎ ሲወሰድ ከመቆየቱ አንጻር፤ የለውጥ ኃይሉ እነዚህን አገራዊ ስብራቶች ለማከም የጀመረው መንገድ ፈታኝ መሆን ብዙም ሊያስገርም አይገባም። በለውጡ ኃይል ላይም ተስፋ ሊያስቆርጥ አይገባም።

እንዲያውም የለውጥ ኃይሉ ስብራቶቹን ለማከም፤ የታሹበትን ማደንዘዣ፣ የታሸጉበትን ፋሻ በማንሳት ስብራቱን ለዘለቄታው በማከም፤ ለመጪው ትውልድ የተሻለች አገር ለማስረከብ እየሄደበት ያለው ፈታኝ መንገድ ሊበረታታና ከፍያለ ድጋፍ ሊሰጠው የሚገባ ነው።

አሁን ላይ እንደ አገር እያንገዳገዱን ያሉት ተግዳሮቶች ዛሬን ከትናንት ስብራቶች ለማከም ከምናደርገው ጥረት የሚመነጩ ከመሆናቸውም በላይ፤ ነገን ብሩህ በማድረግ ሂደት ውስጥ ወሳኝ አቅም ገንብተን እንድንሻገር የሚረዱን ናቸው።

ለውጥ በአንድ ወቅት ተጀምሮ የሚያበቃ ትግል ሳይሆን ቀጣይነት ያለው፤ በጊዜ ሂደት ውስጥ እራሱን እያደሰ በትውልዶች መንሰላሰል ማኅበረሰባዊ ተስፋን የሚያጎናጽፍ ከመሆኑ አንጻር፤ ለውጡ በመጪዎቹ ትውልዶች ተጠናቆ ለአገር የተሟላ ትሩፋት የሚሆን እንጂ ትናንት ላይ ተጀምሮ ዛሬ ላይ የሚያበቃ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዛሬም በጋራ እንድንቆም የሚያስገድዱን በርካታ የቤት ሥራዎች አሉ

በእምነት

ባለፉት ሁለት ዓመታት እንደ አገር ብዙ ችግርና መከራን ለማለፍ ተገደናል። በእርግጥ ይህ ችግርና መከራ በሕዝባችን አንድነትና ርብርብ ፤ በመንግሥት የሰላም አማራጭ መልክ ይዞ አገር አንጻራዊ በሆነ ሰላም ውስጥ ትገኛለች። ይህም ሆኖ አሁንም አንድነታችንን ፤ መደጋገፋችንን እና መተሳሰባችንን የሚፈልጉ በርካታ ችግሮች አሉብን ፡፡

መጪውን ጊዜ ብሩህ ለማድረግ ቀደም ሲል ችግሮቻችንን ለማለፍ ከዳር እስከ ዳር ያሳየነውን አንድነት አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ። እያንዳንዱ ዜጋ እራሱን ፣ ጊዜውን፣ ገንዘቡን እና እውቀቱን ፤ ለአገሩ ያለውን ሁሉ ያለመቆጠብ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

በመላው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለፉት ሁለት ዓመታት ለአገራችን ያለንን ሁሉ አንሰስትም ብለው የሚችሉትን ነገር ከማድረግ ጀምሮ የአገራቸውን እውነት በዓለም አደባባይ ከፍ ብሎ እንዲሰማ ብዙ ለፍተዋል ብዙ ጥረዋል።

በተለይም ጦርነቱን ያመጣብን ጣጣ ለመመከት በፐብሊክ ዲፕሎማሲ፣ የአገርን እውነት በማስረዳት፣ ዜግነቱን ተጠቅሞ ትልልቅ የዓለም ባለሥልጣናት ላይ ጫና በማሳደር ፣ ገንዘቡን በማዋጣት ትልቅ ስራን በመስራት አገሩ ላይ ሊጣሉ የነበሩ ማዕቀቦች ክልከላዎችና ሌሎች እርምጃዎች ሁሉ እንዲቀለበሱ የበኩላቸውን አበርክተዋል።

ይህ ልፋትና ጥረታቸውም ፍሬ አፍርቶ እነሆ አገራችን የከፋ ችግር ውስጥ ሳትገባ ጠላቶቿ ወይም የሷን ክፉ የሚያስቡ ሁሉ እንደተመኙላት ሳትበታተንና ዜጎቿ መግቢያ ሳያጡ ዛሬን ለማየት በቅተናል፡፡

ይህ እንዲሆን ለለፉ ሁሉ ደግሞ ምስጋናን መቸር አዋቂነት ብሎም ኢትዮጵያዊነት ነው። ከዚህ አንጻር መንግሥት መላውን በአገርም በውጭም ያለውን ዜጋውን ቢያመሰግንም ፣ በተለየ ሁኔታ ግን አገራቸውን ከፊት አስቀድመው በባዕድ አገር ለተንከራተቱ አደባባይ ወጥተው ስለያዙት እውነት ለማስረዳት ለጣሩና ውጤትም ላመጡ የዳያስፖራ አባላት የሚመጥን የምስጋና ፕሮግራም ማዘጋጀቱ የሚያስመሰግነው ነው።

በአገርና ከአገር ውጪ የነበሩ ኢትዮጵውያንና ትውልደ ኢትዮጵውያን ባደረጉት ሁለንተናዊ እልህ አስጨራሽ ትግል ዛሬ ላይ እንደ አገር ያሳለፍነውን አስከፊውን ምዕራፍ ዘግተን ወደ እድገት የታሪክ ምእራፍ ተሸጋግረናል፤ ለዚህም በተለይ በባዕድ ምድር የሚኖሩ እህት ወንድሞቻችን ከከፈሉት ዋጋ በላይ ፣ በጋራ የመቆምንም አስፈላጊነትና ጠቀሜታ አሳይታችሁናል ለዚህም መመስገናችሁ ቢያንሳችሁ እንጂ አይበዛባችሁም።

ዛሬ ላይ ችግሩን በሰላም ስምምነት ለመቋጨት ተስፋ ሰጪ መንገድ ላይ ነው ። ይህ አገራዊ ስኬት በጀግኖች ልጆቿ የተገኘ ውጤት ነው፤ በቀጣይ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን በመሻገር የአገርን ክብር ማስጠበቅ የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ነው ፣ ስዚህም በጋራ መቆም ወሳኝ ነው

እንደ አገር ያሳለፍነውን አስከፊው ምዕራፍ ከባድ ቢሆንም አሁን ላይ ግን ሁሉንም በተባበረ ክንዳችን መመከት ችለናል ፤ ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚገባው ትናንት በችግር ወቅት የጀመርነውን አዲስ የትብብር ምዕራፍ ከፍ ወዳለ ደረጃ በማሸጋገር አገርን የተሻለ ተጠቃሚ የምትሆንበትን ሥርዓት መፍጠር ነው።

እንደ አገር አሁንም አሮጌውን ምዕራፍ በዘላቂነት ዘግተን ኢትዮጵያን የሚመጥናት(አሁን ያለውን ትውልድ የሚመጥን) አዲስ የታሪክ ምእራፍ ለመክፈትና አዲስ ታሪክ ለመጻፍ የዲያስፖራው ሁለንተናዊ ተሳትፎ ወሳኝ ነው።

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንጻር ሰሞኑን ለዲያስፖራው ማህበረሰብ የተሰጠውም እውቅና ጤናማ ፉክክርን በመፍጠር የበለጠ ሥራ እንዲሠራ የሚያበረታታ ነው። የሕዝብን ሕይወት ለማሻሻልና የአገርን እድገት ለማረጋገጥ የሚተጉ ሁሉ እውቅና እንደሚገባቸው ያመላከተ ነው።

በእርግጥ አሁን ከባዱን ምዕራፍ ተጋግዘን ያለፍነው ቢሆንም እንደ አገር ዛሬም በጋራ እንድንቆም የሚያስገድዱን በርካታ የቤት ሥራዎች አሉብን ፤ ከነዚህ የቤት ስራዎቻችን መካከል አንድና ዋነኛው የወደሙ የመሰረተ ልማት አውታሮችን መልሶ የመገንባት ስራ ነው። ይህ ስራ የዲያስፖራውን ማህበረሰብ ከፍያለ ርብርብ ይፈልጋል።

ኢትዮጵያ በየዘመኑ ጀግኖችን ታፈራለች። ባለፉት ዓመታት ያጋጠመንን ችግር ለመሻገር በተደረገው ተጋድሎ የጸጥታ አካላትን ጨምሮ በየዘርፉ ተሰልፈው አገሪቱን ያገለገሉ ሚሊዮን ጀግኖች ተፈጥረዋል። የዲያስፖራ አባላትም በተለያዩ የዓለም አደባባዮች የኢትዮጵያን እውነታ ለማስረዳት ያላቸውን ሁሉ አበርክተዋል። ይህን ለአገር የከፈሉት ዋጋ ደግሞ በወርቃማ ብዕር ተጽፎ የሚኖር ይሆናል።

ዛሬ ላይ ችግሩን በሰላም ስምምነት ለመቋጨት ተስፋ ሰጪ መንገድ ላይ ነው ። ይህ አገራዊ ስኬት በጀግኖች ልጆቿ የተገኘ ውጤት ነው ፤ በቀጣይ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን በመሻገር የአገርን ክብር ማስጠበቅ የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ነው ፣ ለዚህም በጋራ መቆም ወሳኝ ነው ።

የዲያስፖራው ማህበረሰብም ለአገራቸው የሚያደርጉትን ሁለንተናዊ ድጋፍ አጠናክረው በመቀጠል አካላቸው ባዕድ አገር ልባቸው ግን ሁሌም ከአገራቸው ጋር መሆኑን ማሳየት መቻል አለባቸው።

ዛሬም ያልተሻገርናቸው በርካታ ችግሮች ከመኖራቸው አንጻር ዲያስፖራው በእውቀት ሽግግር፣ የልማት ሥራዎችና በሌሎች መስኮች ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት አገራችንን ከለሙት አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተጀመረውን ጥረት በበለጠ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል።

መንግሥትም ይህንን አቅም ለመጠቀም ከዚህ ቀደሙ በተሻለ ሁኔታና በተጠና መንገድ የዲያስፖራውን ማህበረሰብ ማስተባበርና መደገፍ ይጠበቅበታል። ይህንንም በተጨባጭ እየሰራ ማሳየት ይኖርበታል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

# የሙርሲዎች የውበት ፍልስፍና

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ውበት ምንድነው? ስለ ውበት ስናስብ በቅጽበት ወደ አዕምሯችን የሚከሰተው ምስልስ ምን ይመስል ይሆን? ስልክክ ያለ አፍንጫ?፣ ጎላጎላ ያሉ አይኖች?፣ ወይንስ እንደ በረዶ የነጡ ጥርሶች ከተንዠረገገ ፀጉር ጋር? በርግጥ በብዙዎች አዕምሮ እና ሥነ ልቦና ውስጥ ውበት የተሳለችው እንደዚህ ነው። ነገር ግን ከዚያ አልፈን የውበትን ዳርቻ እያሰፋን ስንሄድ ደግሞ ውበት እንደ ባህልና እምነት ሆኖ እናገኘዋለን።

በዓለማችን ላይ ውበትን የምንገልጽበት መንገድ በብዛት ተመሳሳይ ቢሆንም፤ በራሳቸው የባህልና ውበት ፍልስፍና ውስጥ የሚኖሩ ጥቂት ጎሳዎች ይገኛሉ። የኛው አገር ሙርሲዎች ለዚህ አንድ ምሳሌ ናቸው። ባህላዊ ቁሶችንና አልባሳትን የሚጠቀሙት ቱባ ባህሎች በየዘመናቱ የሥልጣኔ አብዮት እየገረሰሳቸው አሁን ከተረፉት በጣት ከሚቆጠሩ ጥቂት ጎሳዎች መሃል ሙርሲዎች ተጠቃሽ ናቸው። ሙርሲዎች ምናልባትም እርቃናቸውን ለመሸፈን ያህል ከወገባቸው ላይ እራፊ ጨርቅ ጣል አድርገው ያለመተፋፈር ሲሄዱ፣ ከዘመናዊው ዓለም መዘውር ውጭ የሆኑ መስሎ ይሰማን ይሆናል። እውነታው ግን ይህ አይደለም፣ ከዚህም ከዚያም የተለየ ነው። እነርሱ በውበት አድማስና ደሴት የሚኖሩ የተለዩ ናቸው።

በሰውነታችን ላይ አንዲት ቁስል እንዳታርፍ በዘመናዊ ኬሚካሎች ቆዳችንን በምንፈትግበት በዚህ አርቴፊሻል ዘመን እነርሱ ግን ከንፈሮቻቸውን ተልትለው ሸክላ ያንጠለጥሉበታል፤ ጆሮዎቻችንን በስተን ወርቃማ አሊያም ብራማ ጉትቻ በምናንጠለጥልበት በዚህ የብልጭልጭ ዓለም፣ እነርሱ ግን ጆሮዎቻቸውን እስከ ትከሻቸው ዘርጥጠው ክብ ሸክላ ይወጥሩበታል። ይህንንም ስናይ ኋላ ቀር እብደት እያበዱ እንደሆነ ከማሰባችን በተጨማሪ በነገሩ ስቅቅ ልንልም እንችላለን። እነርሱ ግን ደስታና እርካታ የሚያገኙት በዚህ ነው።

የሙርሲዎች ልዩ የባህል ውበት መገለጫ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ የሴቶች የከንፈር ላይ የሚንጠለጠል ሸክላ ነው። አንዲት የሙርሲ ሴት ይህን የከንፈር ላይ ሸክላ ስታንጠለጥል የራሱ የሆነ ምክንያትና ትርጉም አለው። በሙርሲዎች ባህል አንዲት ሴት እድሜዋ ወደ 16 ሲጠጋና ለአቅመ ሄዋን ስትደርስ ከንፈሯን የመተልተልና ሸክላ የማንጠልጠል ሥርዓት ታከናውናለች። በአብዛኛው ይህን ሃላፊነት የምትወስደው የልጅቷ እናት ስትሆን የሚተለተለው ከንፈር የሚለጠጥበት ስፋት የሚወሰነው ግን በልጅቷ ፍላጎት ነው፡፡ በዚህ መልኩም ሂደቱ ይጀመራል። በመጀመሪያ ከንፈሯን የማለስለስና የመለጠጥ ስራ ይሰራል። ልጅቷ የምትፈልገው የከንፈር መጠን ላይ እስኪደርስም እለት እለት በተለያዩ ዜዴዎች እንዲሰፋ ይደረጋል። ከዚህ በኋላ የልጅቷ የፊት ጥርስ ይነቀላል። ምክንያቱ ደግሞ ጥርሷ ለሸክላው ምቾትን እንዳይነሳው ሲባል ነው። በመቀጠልም በክብ ቅርጽ የተሰራ ሸክላ ይዘጋጃል። በአብዛኛው ሸክላው የሚዘጋጀው ከእንጨት እና ከአፈር ነው። የከንፈሯ ቅርጽና መጠን በሚፈለገው ልክ ሲሆን ልጅቷ የሙርሲ ቆንጆ ስለመሆኗ ምልክት የሆነውን ክብ ሸክላ በከንፈሯ ላይ እንዲንጠለጠል ይደረጋል። ይህንን ሁሉ ሂደት አልፋ ሸክላውን ለማንጠልጠል በርካታ ወራትን ሊፈጅባትም ይችላል።

ይህ የሙርሲ ሴቶች በከንፈራቸው ላይ የሚያንጠለጥሉት ክብ ሸክላ ከውበት መገለጫነት አልፎ በርካታ ትርጉሞች አሉት። ለምሳሌ ሴቶቹ ካገቡ በኋላ ለባሎቻቸው ምግብ በሚያቀርቡበት ሰዓት ይህንን ሸክላ በከንፈራቸው ላይ በማንጠልጠል ነው፤ ትርጉሙ ደግሞ ለባሏ ትልቅ ፍቅርና ክብር ከሙሉ ቁርጠኝነት ጋር እንዳላት ያንጸባርቃል። ሴቷ ድንገት ባሏ በሞት የተለያት እንደሆን የዚህች ሴት ውጫዊ ውበቷ ከባሏ ጋር አብሮ ወደመቃብር ወርዷል ተብሎ ይታመናል። ውበቷም ረግፏል ተብሎ ስለሚታሰብ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሸክላውን ማድረግ ታቆማለች። ከዚህ ውጭ ግን በገበያም ሆነ በየትኛውም ስፍራ በምትንቀሳቀስበት ሁሉ አድርጋው ትሄዳለች። ምናልባት ይሄን የማታደርግ ሴት የሙርሲ ጎሳ አባል እንዳልሆነች ተደርጋ ልትቆጠርም ትችላለች።



ሌላው የሙርሲ ሴቶች የከንፈር ላይ ሸክላ አስገራሚው ነገር፤ የሸክላው መጠን በጨመረ ቁጥር የልጅቷ ተፈላጊነትም የሚጨምር መሆኑ ነው። ወንዱ በሚያገባት ሰዓት ለቤተሰቦቿ የሚሰጠውን የከብት ጥሎሽ በዚያው መጠን ከፍ ያደርገዋል። እሷም ለቤተሰቦቿ የሀብትና የክብር ምንጭ ትሆናለች። ትልቅ ሸክላ ያደረገችን ሴት ቤተሰቦቿ ብቻ ሳይሆኑ ማህበረሰቡም እንደ እንቁላል ይንከባከባታል። ይህን ግርማ ሞገስና የበላይነትን ለማግኘትም እርስ በእርሳቸው ይፎካከራሉ። በፈረንጆቹ 2014ዓ.ም አብርሃም ጆፍ የተባለ አውስትራሊያዊ የፊልም ሰሪ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ካነሳቸው ፎቶግራፎች መሃከል አንድ ለየት ያለ ፎቶግራፍ በማህበራዊ ሚዲያዎች አሰራጨ። በዚህ ፎቶ ግራፍ ላይ የነበረችው አጣዬ ኢሊጊዳኜ የተባለች ሴት ስትሆን በከንፈሯ ላይ ትልቅ ሸክላ አንጠልጥላ ትታያለች። ሸክላው 15.9 ሴ.ሜ ሲሆን በክብረ ወሰን ተይዞላት ነበር።

ታዲያ በዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ አልፋ የመጣችን የሙርሲን ሴት ማንኛውም ወንድ ዝም ብሎ አያገባትም። ወንዱም ሌላ ፈተና ይጠብቀዋል። የሙርሲ ወንዶች ወንድነታቸውን የሚያስመሰክሩት በዶንጋ ሥርዓት ወይንም በዱላ ፍልሚያ ሲሆን ውበታቸውን የሚገልጹት ደግሞ ከፊታቸው ላይ ነጭ ቀለም በመቀባት ነው። ያቺን ቆንጆ ሴት ለማግባትም ወንዱ እነዚህን ሁለት ነገሮች ከሌሎች በተሻለ መንገድ መከወን ይኖርበታል። ፈተና፣ እምነት፣ ጽናት በመጨረሻም አሸናፊነት የሙርሲዎች መለያ ነው። ያልተበረዘና ያልተመረዘ ንጹህ ባህላቸውን ውበትና ጌጣቸው አድርገውት ዓለምን ሁሉ አጀኢብ አሰኝተውታል። ለዚህም ማሳያ ብዙ ብሮችን እየቀፈቀፉ ወደ አገራችን የሚፈሱት ቱሪስቶች የሙርሲዎችን መንደር ሳይጎበኙ አይሄዱም። በሚያዩት ነገር ሁሉም ሳይገረሙና ሳያደንቁ አያልፉም። እዚያ መንደር ላይ እውነተኛ ውበት ስለመኖሩም ይመሰክራሉ። እኛስ? እንዴት ይሆን የምንቀበለው፣ አሁንም ውበት ማለት ጥቁር ሀር መሳይ ጸጉር፣ ሰልካካ አፍንጫ፣ ተረከዘ ሎሚ ብቻ ነው፤ እያልን ከገደብነው አንበሳ ለምን ስጋ ብቻ ይበላል የሚል ጥያቄ እንደማንሳት ይሆንብናል። ተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ ውስጥ ያደረ፣ የሚታይ ነገር ግን እኛ የማንረዳው ልዩ ምርጫ መኖሩን መዘንጋት የለብንም። የሙርሲዎች ውበት የእነርሱ ብቻ ሳይሆን የኛም ጭምር መሆን በመቻሉ ባንከተለውም ልናደንቅና ልንጠብቅ የግድ ይለናል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

# ከሕግም ከአመክንዮም የተጣሉ የድርጅት ስያሜዎች

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ በወራሪ ቅኝ ገዢዎች እጅ ባለመውደቋ ከጠቀሟት ነገሮች አንዱ ባህሏንና ቋንቋዎቿን ጠብቃ መኖር መቻሏ ነው። አሁን አሁን ግን የባእድ አገር ቋንቋና ባህል መልኩን ቀይሮ በተለያዩ መንገዶች ተገዢ እያደረገን እንደመጣ ብዙ መከራከሪያ ነጥቦች አሉ። ከነዚህ መካከል አንዱ በተለይም እንደ አዲስ አበባ ባሉ ትልልቅ የአገራችን ከተሞች የንግድ ድርጅት ስሞች ዋነኛ ማሳያ ናቸው።

በበርካታ የኢትዮጵያ ከተሞች ከሚሰጡት አገልግሎትና ከሚኖሩበት ማህበረሰብ አኳያ አንጀት አርስ የሆኑ ምስጉን ስያሜ ያላቸው ድርጅቶች ጥቂት አይደሉም። የዛሬው ትዝብታችን ግን ከነዚህ በተቃራኒ ግራ ገብቷቸው ግራ የሚያጋቡን ከሕግም ከአመክንዮም የተጣሉ የንግድም ይሁን ሌሎች የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ስያሜዎች ላይ ትኩረት አድርጓል።

እውነት ለመናገር የአንዳንድ ድርጅት ስሞች ከሚሰጡት አገልግሎትና ከሚያገለግሉት ማህበረሰብ አኳያ ምንም ትርጉም የሌላቸው ከመሆናቸው ባሻገር ለባለቤቱ ራሱ ትርጉም ያላቸው አይደሉም። መቼም ለአንድ ነገር ስም ወይም ስያሜ ሲሰጥ ካለምክንያት አይደለም። በአገራችን ለልጆች እንኳን ሳይቀር ስም ሲወጣ በምክንያት ነው። ስም መጠሪያ ከመሆኑ ባሻገር በማንነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል የሚል አመለካከትም አለ፡፡ ስም አንድ ነገር ካለፈም በኋላ ይኖራል፡፡ በዚህ ምድር የአንድ ዘመን ነዋሪነት አሻራ ነው፡፡ ሰዎች ሲተዋወቁ፣ ስለእነሱ ሲወሳ፣ የእነሱ የሆኑ ነገሮች ሲገለጹም መጠሪያቸው ቦታ አለው፡፡ መለዮም ነው፡፡ በከተሞቻችን ብዙዎቹ በተለይም የንግድ ድርጅቶች ስያሜ በምክንያት የተሰጠ መሆኑ አከራካሪ ነው።

> **መቼም ለአንድ ነገር ስም ወይም ስያሜ ሲሰጥ ካለምክንያት አይደለም። በአገራችን ለልጆች እንኳን ሳይቀር ስም ሲወጣ በምክንያት ነው። ስም መጠሪያ ከመሆኑ ባሻገር በማንነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል የሚል አመለካከትም አለ፡፡ ስም አንድ ነገር ካለፈም በኋላ ይኖራል**

ትርጉም የለሽ የድርጅት ስያሜዎች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ወደ ሌሎች አገራት ቋንቋ በተለይም እንግሊዝኛ በብዙ እያዘነበለ መምጣቱን ትንሽ በከተሞች ዞር ዞር ብሎ መመልከት በቂ ነው። አስገራሚው ነገር በርካታ ድርጅቶች ስያሜያቸው እንግሊዝኛ መሆኑ አይደለም። ስማቸው በእንግሊዝኛ ሆኖ ትርጉሙም ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር አለመገናኘቱ ግራ አጋቢ ነው። አንዳድ ድርጅቶች በተለይም ትልልቅ ሆቴሎች ስያሜያቸው በእንግሊዝኛ መሆኑ ምናልባትም በብዛት አገልግሎት የሚሰጡት የውጭ ዜጎችን በመሆኑ በቀላሉ እንዲያዙ ሊሆን ይችላል ብለን እናስብ። ያም ሆኖ ትልልቅ ሆቴሎች ሁሉ የግድ ስማቸው በውጭ ቋንቋዎች ይሁን የሚል መከራከሪያ በራሱ ብዙ ርቀት ሊያስጉዝ አይችልም። እሺ ትልልቆቹን ወይም ዓለም አቀፍ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን እንተዋቸው፣ ትንንሽ ሻይ ቤቶችና የንግድ ድርጅቶች አገልግሎት የሚሰጡት ለእኛው ሆኖ ሳለ የውጭ ቋንቋዎች ላይ መንጠልጠላቸው ምን የሚሉት ነው?

ሌላው አስገራሚ ነገር ከአገር ውስጥም ከውጭም ቋንቋዎች በተውጣጡ ሁለት ቃላት የሚሰየሙ ድርጅቶች ናቸው። በዚህ መንገድ ስም የወጣላቸው አብዛኞቹ ድርጅቶች የበለጠ ትርጉም የለሽ ከመሆናቸው በላይ ከሕግም የተጣሉ ናቸው። ከሁለት አንዱን ቋንቋ ቢጠቀሙ እንኳን የተሻለ ነው። እንዲያውም የአገር ውስጥ ቋንቋውን ብቻ ቢጠቀሙ ከትርጉምም ከስያሜው ውበትም አኳያ የተሻለ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። ለምሳሌ ያህል “ሲስተር፣ ብራዘርስ” ተብለው የሚሰየሙ በርካታ ድርጅቶች አሉ። አሁን እንዲያው ሲስተርስ ወይም ብራዘርስ የሚለው ስያሜ ትርጉሙ ሳይለወጥ በአገራችን ቋንቋ እህትማማቾች ወይም ወንድማማቾች ተብሎ ቢሰየም የተሻለው የትኛው ነው? በሚገርም ሁኔታ ይህንኑ ሲስተርስ ወይም ብራዘርስ የሚል ስያሜ ከሌላ ቋንቋ ከተመነተፉ ቃላቶች ጋር አዳብሎ የሚሰይሙም አልጠፉም። ሲስተርማማቾች ወይም ብራዘርማማቾች የሚሉ ግራ የገባቸው የድርጅት ስያሜዎች ገጥመውኝ ያውቃሉ።

የቋንቋውን ነገር እንተወው፣ በማህበረሰባችን ፊት ለፊት የማይጠሩ (ታቡ) ቃላትን ጭምር የሚጠቀሙ የድርጅት ስሞች አሉ። እነዚህን ድርጅቶች ለምሳሌ መጥቀሱ በነፃ ማስታወቂያ መስራት እንዳይሆንብኝ ትቼዋለሁ። ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ሕጉ ምን ይላል የሚለውን እንመልከት። ከንግድ ሚኒስቴር የድርጅት ስያሜ መመሪያ ጥቂቶቹ ይህን ያስቀምጣሉ “ ከሌሎች አገራት፣ዓለምአቀፍ ወይም አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የተያያዙ ስሞች መሆን የለባቸውም፣ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ ድርጅት ወይም ማህበረሰብ፣ ጎሳ፣የሰራተኛ ማህበራትና የህብረት ስራ ማህበራት ጋር የተያያዘ መሆን የለበትም። የአገር መሪዎች፣ የታላላቅ ታዋቂ ሰዎችና ዓለም አቀፍ ትልልቅ ከተሞች ስሞች ለንግድ ስም ሊውሉ አይችሉም። የንግድ ስም የሁለት አገሮችን ስሞች በአንድ ላይ የያዘ መሆን የለበትም ለምሳሌ (ኢትዮ ካናዳ)”።

ከነዚህ መመሪያዎች አኳያ የድርጅት ስሞችን ከታዘብን በርካታ ድርጅቶች እንዴት ፍቃድ ሊያገኙ እንደቻሉ አስገራሚ ነው። ለምሳሌ ያህል ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታዎችን ታከው በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በታዋቂ ፖለቲከኛ ስም የሚሰየሙ ትንንሽ ድርጅቶች በየቦታው መፈልፈላቸውን በሆነ አጋጣሚ ሳንታዘብ አንቀርም። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ በሌሎች አገር መሪዎች ስም ሻይ ቤቶች፣ ቁርስና ምግብ ቤቶች ሳይቀሩ ተሰይመው ሲሰሩ መመልከት የተለመደ ነው። በዚህ ረገድ እንደ ቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ በርካታ ትንንሽ የንግድ ድርጅቶች የተሰየመለት የአገር መሪ ያለ አይመስለኝም። እዚህ ጋር አንድ ፈገግ ያደረገኝን ስያሜ ላንሳ፣ “ቢዮንሴ ቁርጥ ቤት” ይላል ስያሜው፣ ቁርጥን ከዝነኛዋ አሜሪካዊት አቀንቃኝ ቢዮንሴ ጋር ምን እንደሚያገናኛቸው ራሱ ሰያሚው ምክንያት ይኖረው ይሆናል ብዬ ባወጣ ባወርድ ሊገለጥልኝ አልቻለም።

የሆነው ሆኖ እንዲህ አይነት ከሕግም ከምክንያታዊነትም የተጣሉ የድርጅት ስያሜዎች ሲወጡ የአውጪው ብቻ ሳይሆን የፈቃጁም አካል ችግር ገዝፎ እንደሚታይ ማንሳቱ ተገቢ ነው። አንድ ድርጅት ወደ ስራ ከመግባቱ አስቀድሞ የንግድ ፍቃድ ሲያወጣ የድርጅት ስያሜ ጉዳይም አብሮ መነሳቱ አይቀርም። በዚህ ረገድ ከሕግ አኳያ መመሪያው የማይፈቅድላቸው ስያሜዎች የሚሰጡት በችልተኝነት ወይም በዘፈቀደ ነው ማለት ነው። ካልሆነ ደግሞ ብዙ ድርጅቶች ከሕግ እውቅና ውጪ ነው የሚሰሩት እንደማለት ነው።

# ነፃ ሃሳብ

# በአዲስ የትምህርት ሥርዓት አዲስ ትውልድ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)**

በዛሬ ጽሁፌ አዲስ ትምህርት፣ አዲስ አገር፣ አዲስ ትውልድ ስል መጥቻለሁ። ትምህርት አገርና ትውልድ የሚቀረጹበት ቁልፍ ነው። እንደሚታወቀው አገራችን ጥሩ የትምህርት ሥርዓት ከሌላቸው የዓለም አገራት ውስጥ ቀዳሚዋ ናት። ይሄ ለምን ሆነ ብለን ስንጠይቅ ከመማር ማስተማር ጋር የተያያዙ ችግሮችን ነው የምናገኘው።

የመማር ማስተማር ሥርዓታችን ለኩረጃ የተጋለጠ ከመሆኑም ባለፈ ለትምህርት ጥራት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር አይደለም። ለበርካታ ዓመታት በአንድ አይነት መንገድ ስንማርና ስናስተምር ቆይተናል። ይሄ ለውጥ የሌለው የመማር ማስተማር ሥርዓት ደግሞ አዲስ አገር፣ አዲስ ትውልድ መፍጠር ተስኖት በትምህርት ረገድ ኅስቋላዋን ኢትዮጵያ አስታቅፎናል፡፡

በርግጥ አገራችን ውስጥ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ብዙ ኮሌጆች አሉ እኚህ ሁሉ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ግን ለአገራችን የሚገባውን እውቀትና ሽግግር አልሰጧትም። ጥራትና ብቃት ካልታከለበት የዩኒቨርሲቲ መብዛት ብቻውን ዋጋ የለውም። አሁን አገራችን ያጣችው ዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ ሳይሆን እውቀትን መሰረት ያደረገ የመማር ማስተማር ሥርዓት ነው፡፡

አሁን እንደ አገር ያጣነው ከኩረጃ የራቀ አንብቦና ተረድቶ ለራሱም ሆነ ለሌሎች የሚተርፍ ተማሪን ነው። አሁን አገራችን ያጣችው ሃላፊነት የሚሰማው፣ ተምሮና አውቆ ለአገር የሚጠቅም ዜጋ ነው ። ተማሪዎች ኮርጀው ካለፉ፣ ኮርጀው ስራ ከያዙ አገር የምታተርፈው ትርፍ የላትም። እንደ አገር ትርፋችን ያለው እውቀትን መሰረት ባደረገ የመማር ማስተማር ሥርዓታችን ውስጥ ነው። እንደ አገር ትርፋችን ያለው ለውጥ በሚያመጣ፣ በእውቀትና ቴክኖሎጂ በታገዘ የተማሪና መምህር መስተጋብር ነው፡፡

እንደመንግሥት የያዝናቸው የእድገትና የልማት እቅዶች የሚሰምሩት አስተማማኝ የትምህርት ሥርዓት ሲኖረን ነው። በእውቀት የሚመራ የትምህርት ሥርዓትን ሳንገነባ አገርና ትውልድ መፍጠር አይቻለንም። አሁን ላይ ተምረን ሥራ የምንጠብቀው፣ ሥልጣን ይዘን አገርና ሕዝብ የምንዘርፈው ጥራት በሌለው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ስላለፍን ነው።

እውቀት ሁልጊዜም ከመፍትሄ ጋር የተቆራኘ ነው። በእውቀት የታገዘ ትምህርት ሥራ ፈጥሮ ይሰራል እንጂ ጠባቂ አይሆንም። በእውቀት የተገኘ ሥልጣን ለማህበረሰቡ ችግር ፈቺ ይሆናል እንጂ ከማህበረሰቡ አይሰርቅም። በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው እያየናቸው ያሉ ነውሮች ደካማ ከሆነ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የተወለዱ ናቸው፡፡

አገራችንን ከዘመናዊው ዓለም ጋር ለማስተዋወቅ ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው። እርሱም ጥራት ያለውን ትምህርት ለማህበረሰቡ ማዳረስ ነው። በሁሉም መስክ የተሻለችውን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ከኩረጃ ነጻ የሆነ እውቀትን መሰረት ያደረገ የመማር ማስተማር ሥርዓት ያስፈልገናል፡፡

እስኪ እንጠይቅ እስካሁን የመጣንበት የትምህርት ሥርዓታችን ምን አተረፈልን? በየአመቱ የሥራ አጥ ቁጥር እየጨመረ ነው። በየአመቱ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥር የትየሌለ ነው። ተምረን ለማህበረሰቡ ለውጥ ካላመጣን፣ ተምረን የማህበረሰቡን ችግር መፍታት ካልቻለን የመማር ጥቅሙ ምንድ ነው?። እውቀት አገራዊ ችግሮችን መፍቻ ትልቁ አቅም ነው።

ታላላቆቹን አገራት እንዴት ሰለጠኑ ብለን ስንጠይቅ መጀመሪያ የምናገኘው እውቀት መር የሆነ የትምህርት ሥርዓት ስለነበራቸውና ስላቸው ነው። እኛም አገርና ትውልድ የሚፈጥር እውቀት መር የሆነ የትምህርት ሥርዓት ያስፈልገናል። የምናሽሞነሙነው ነገር የለም። ስር ነቀል የሆነ ለውጥ ያስፈልገናል። እንደ አገር ከኩረጃ የጸዳ ትውልድና እውቀት ያሻናል፤ አውቆና ተረድቶ ፈተና ያለፈ ተማሪ ያስፈልገናል። እንደ አገር ኩረጃን የሚጸየፍ ማህበረሰብ መፍጠር አለብን፡፡

ያለፍንባቸውን ሰላሳ የመማር ማስተማር ዓመታት መለስ ብለን ብናያቸው በትምህርቱ ዘርፍ ይሄ ነው የሚባል ለውጥ አላመጣንባቸውም። ለውጥ በሌለው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ነበርን ማለት ይቻላል። ይሄ ብቻ አይደለም በየአመቱ ከፈተና ጋር በተያያዘ የምንሰማቸው የስርቆት ወሬዎች በተማሪዎቹም ላይ ሆነ በትምህርት ጥራቱ ላይ ከፍተኛ ጫና ሲያሳድር እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡

አሁን ላይ ትምህርት ሚኒስቴር በዘርፉ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመቅረፍ ከሄደባቸው ርቀቶች ውስጥ የመጀመሪያው የተለመደውን የተማሪዎች የአፈታተን ዘዴ መቀየር ነበር። በዚህም መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ጊቢ ውስጥ እንዲፈተኑ ተደርጓል። ይሄ መሆኑ እንደአገር የሚጠቅመው ብዙ ነገር አለ።

በመጀመሪያ ደረጃ የተማሪዎችን መኮራረጅ ከማስቀረቱም ባለፈ በትምህርት ጥራት ላይ የጎላ ድርሻ ያመጣል። ልክ እንደዚህ አገራችን የአቅጣጫ ለውጥ ነው የሚያስፈልጋት። በአንድ አቅጣጫ ተጉዘን ውጤት ያላመጣንባቸው ብዙ የስራ መስኮች አሉ። ትንሽ ዞር ማለት ይጠበቅብናል፡፡

ተማሪዎች በቅርቡ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ፈተናቸውን ወስደው ውጤታቸውንም አይተዋል። ከውጤት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ታሪክ ብዙዎችን ያስደነገጠ ውጤት ይፋ ተደርጓል። ፈተናውን ከወሰዱ ስምንት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ አምስት መቶ ሃያ ተማሪዎች (896,520) ውስጥ ከግማሽ በላይ ያመጡት ሃያ ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ (29,909) ተማሪዎች ብቻ መሆናቸው ተገልጿል።

**ከዘንድሮ ውጤት ጋር በተያያዘ የተስተዋለው ሌላው አስገራሚ ነገር በአገሪቱ ከሚገኙ ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ ሺ አንድ መቶ ስልሳ አንድ (1161) መደበኛ ትምህርት ቤቶች አንድም ተማሪ አለማሳለፋቸው ነው**

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሃምሳ በመቶ በላይ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ በሚቀጥለው አመት በቀጥታ ወደዩኒቨርሲቲ ገብተው የአንደኛ ዓመት ተማሪ የሚሆኑበትን አዲስ አሰራር ዘርግቷል። ከዚህም ባለፈ ከሃምሳ በታች ያገኙ ተማሪዎች ውጤት ባላመጡባቸው ውጤቶች አካባቢያቸው በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ድጋፍ ተሰጥቷቸው በቀጣይ ማለፍ ከቻሉ የአንደኛ ዓመት ተማሪ ሆነው እንደሚቀጥሉ አመልክቷል።

ከዘንድሮ ውጤት ጋር በተያያዘ የተስተዋለው ሌላው አስገራሚ ነገር በአገሪቱ ከሚገኙ ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ ሺ አንድ መቶ ስልሳ አንድ (1161) መደበኛ ትምህርት ቤቶች አንድም ተማሪ አለማሳለፋቸው ነው። በዚህ አያበቃም ከአጠቃላዩ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት (1798) የሚሆኑት ትምህርት ቤቶች አንድ ተማሪ ብቻ ያሳለፉ ሆነው ተገኝተዋል።

ከዚህ በተጻራሪም ሰባት የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ያስፈተኗቸውን ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ማሳለፋቸውን በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ተገልጿል። ከዚህ እውነት በመነሳት የአገራችንን የትምህርት ሥርዓት ምን እንደነበረ በድፍረት መናገር ይቻላል።

ከአዲሱ የትምህርት ሥርዓት በፊት እጅግ ብዙ ተማሪዎች የብሄራዊ ፈተናን አልፈው ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ነበሩ። ይሄ እንዴት ሆነ ብለን ስንጠይቅ እጅግ የቀለለ መልስ ነው የምናገኘው። ያም ተማሪዎች በመኮራረጅ ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባቸውን ውጤት ሲያገኙ እንደነበር መረዳት አይከብድም፡፡

አዲሱ የትምህርት ሥርዓት የኢትዮጵያን መጻኢ እድል ከመወሰኑም ባለፈ እውቀትን ብቻ መሰረት ያደረገ የትምህርት ሥርዓትን ይፈጥራል፤ በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎችን ከማፍራት ረገድም የላቀ ሚና ይጫወታል የሚል እምነት አለ። ሌላም መጥቀስ ይቻላል። አዲሱ የብሄራዊ ፈተና አሰጣጥ መንገድ ተማሪዎች ለመኮራረጅ እድል የማያገኙበት ስለሆነ በእውቀትና ራስን በመቻል ተገንብተው ወደ ፈተና ክፍል እንዲገቡ በማድረግ በኩረጃና በትምህርት ጥራት ማነስ የሚታማውን የትምህርት ሥርዓት ይቀይረዋል ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል ።

አንዳንዶች ዝቅተኛ ውጤቱ የተመዘገበው ተማሪዎች ከቤተሰብ ርቀው በአዲስ ቦታ፣ በአዲስ አካባቢ በመፈተናቸው ነው ሲሉ ይሰማል። የትምህርት ሚኒስቴር አሰራሩ አዲስ ከመሆኑ አንጻር የተማሪዎችን ውጤት ከግንዛቤ አስገብቶ የመቁረጫ ነጥብን ዝቅ ቢያደርግ መልካም ነው የሚሉና ሌሎችንም አስተያየቶች እየሰጡ ነው። ጉዳዩንም የፖለቲካ ይዘት ለማላበስ የሚሞክሩም አሉ።

በዚህች አገር ባህል እየሆነ የመጣው ጥሩ ሲሰራ፤ ጮኸን መጥፎ ሲሰራም ጮኸን ፤ለትችትና ለአሉባልታ የመፍጠናችን እውነታ ልጓም የሚያስፈልገው ነው። ለብዙ ጊዜ በትምህርት ጥራት ማነስ ስትጎሳቆል የነበረችው አገራችን መፍትሄ መጣላት ባልን ማግስት እንዲህ አይነት ያልተገባ አሉባልታ ተገቢ አይደለም ።

ለሀገራችን እድገትና መሻገር ሁላችንም ከመንግሥት እኩል ድርሻ አለብን። በጎ ነገር ማዋጣት ባንችል እንኳን ተስፋ አስቆራጮች መሆን የለብንም። በየትኛውም ሚዛን ብንመዝነው አሁን ላለችውም ሆነ ነገ ለምትፈጠረው ኢትዮጵያ የሚበጃት እንዲህ ያለው ከኩረጃ ነጻ የሆነ የትምህርት ሥርዓት ነው፡፡

ተማሪ ለምን ጥሩ ውጤት አላመጣም ብሎ መንግሥትን መጠየቅ ተገቢ ነው ብዬ አላስብም። እርግጥ አገራችን የነበረችበት ሁኔታ ይታወቃል። ያ ሁኔታ ግን ለተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል ብቸኛው ምክንያት ነው ብዬ አላስብም። በቃ የለመድነውና ስንኮርጅና ስናስኮርጅበት የነበረው መንገድ ተዘጋብንና ውጤት ማምጣት አልቻልንም፡፡

በአዲስ የትምህርት ሥርዓት የቻልነውን እንድንሰራ አስገዳጅ ሥርዓት በመፈጠሩ የሚገባንን ውጤት አገኘን። ከዚህ ውጪ ሌላ ምንም አይነት ምክንያት የለውም። ሁልጊዜ አዲስ ነገር የሚያስፈራን ሕዝቦች ነን። ድህነትን እንጠላለን፣ ኋላ ቀርነትን እንጸየፋለን፤ መፍትሄ የሚሆን ነገር ስናመጣ የመፍትሄው አንድ አካል ከመሆን ይልቅ ለትችትና ለወቀሳ የምንፈጥን ነን፡፡

በየትኛውም ሁኔታ ቢታይ አሁን ያለችውን ኢትዮጵያ ለመታደግ የትምህርት ሚኒስቴር አካሄድ እጅግ አዋጪ አካሄድ ነው። የእኛ ጥያቄ ሊሆን የሚገባው ውጤት ያላመጡ ተማሪዎች እጣ ፈንታ ምንድነው? ውጤታቸውን አሻሽለው የተሻለ የትምህርት እድል የሚያገኙት እንዴት ነው? ብሎ መጠየቅ እንጂ ተማሪዎች ለምን ወደቁ፣ ለምን ጥሩ ውጤት አላመጡም ብሎ ወቀሳ ማቅረብ አይደለም፡፡

ገና በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት የዩኒቨርሲቲ የመውጫ ፈተና አለ። ተማሪዎች ከኩረጃ ነጻ በሆነ መንገድ ተፈትነው ዩኒቨርሲቲ ከገቡ በኋላ በመውጫ ፈተና ወደ ሥራ ዓለም ሲገቡ ያኔ የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር በሚያስተማምን መንገድ ላይ እንሆናለን። ወደሚበጀን ማየት አለብን፡፡

አዲሷ ኢትዮጵያ የሚበጃት እንዲህ ያለው ከኩረጃ ነጻ የሆነና በእውቀት የተመራ ትውልድን ማፍራት ነው። ለበርካታ ዓመታት በአንድ አይነት መንገድ ላይ ስንጓዝ ነበር። በአንድ አይነት ሥርዓት አንድ አይነት ተማሪ አስተምረን ስናስመርቅ ነበር። በአንድ አይነት ሥርዓት አንድ አይነት አገር፣ አንድ አይነት ትውልድ ስናፈራ ነበር። የአቅጣጫ ለውጥ ያስፈልገናል፤ በእውቀት አገርና ትውልድ የተቆራኙበት ለውጥ፡፡

# የግብርና ሜካናይዜሽንን ሙሉ ለሙሉ መተግበር እስከ መቼ?

**ስምስም መንግሥቱ**


በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው የግብርናው ዘርፍ አሁንም የመሪነቱን ሚና ይዞ ቀጥሏል። በ2015 በጀት ዓመት ስድት ወር በዋና ዋና ማክሮ ኢኮኖሚ እቅድ አፈጻፀም ላይ በተደረገ ውይይት ግብርናው በተሻለ አፈፃፀም ላቅ ያለ ሆኖ መገኘቱ መገለጹ ይታወሳል። ግብርናው እንዲሸጋገር (ትራንስፎርም) እንዲያደርግ መንግሥት በልዩ ትኩረት የሰራው ሥራ ውጤት እንደሆነም ከተከናወኑት ተግባራት መገንዘብ ይቻላል። ከዋና ዋና ተግባራቶች መካከልም ዘርፉ በግብርና ሜካናይዜሽንን እንዲታገዝ የተሰራው ሥራ አንዱ ሲሆን፣ ለተከታታይ አራት ዓመታት የተከናወነው የበጋ ቆላ መሥኖ ልማትም ግብርናው ከፍ እንዲል ካደረጉት ተግባራት ይጠቀሳል። የበጋ መስኖ ልማቱ ግብርናው እንዲነቃቃ ያስቻለ እንደሆነም ይታመናል፡፡

መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት ልክ በሰፊው አቅዷል። በሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ በቅርቡ በተያዘው የሌማት ቱሩፋት እቅድ ደግሞ በእንስሳትና እንስሳት ውጤቶች፣በንብ ማነብ ሥራዎች እንዲሰሩ አቅጣጫ ተቀምጧል። የግብርናው ሥራ ክረምት ከበጋ እንዲከናወን በማድረግም በክረምት ላይ ብቻ ያተኮረውን የግብርና ሥራ ባህል በመቀየር የትኩረት ሥራው አስተዋጽኦ አድርጓል። በተለይም የግብርናው የመአራረት ዘዴ ኋላ ቀር ሆኖ መቆየት እንዲሁም ለልማቱ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ከመሆን ጋር ተያይዞ እየለማ ያለው መሬትም ካለው ለልማት ሊውል ከሚችለው የመሬት የሀብት መጠን ጋር የተጣጣመ እንዳልሆነ በማሳያነት ይነሳል፡፡

ዘርፉን በግብርና ሜካናይዜሽን ለመደገፍ የተጀመረው ሥራ ከልማት ውጭ ሆኖ የቆየውን መሬት ወደ ልማት በማስገባትም ድርሻ እንዳለው ከዘርፉ ባለሙያዎች ይሰማል። መሬትን ወደ ልማት ከማስገባት በተጨማሪ መንግሥት በሰፊው አቅዶ እያከናወነ ያለውን የግብርና ሥራ ውጤታማ ማድረግ የሚቻለው የግብርና ሜካናይዜሽን ትግበራ ሲጠናከር እንደሆነ እሙን ነው። እኛም በጉዳዩ ላይ የዘርፉ ባለሙያዎች ሙያዊ ትንታኔ እንዲሰጡ ጋብዘናል፡፡

እንግዳችን ዶክተር ይፍሩ ታፈሰ፣ እንደ ባለሙያ ብቻ ሳይሆን፣ የግብርናውን ሥራ በተግባር ለማየትም ጥረት እንደሚያደርጉ ነው የነገሩን። በአሁኑ ጊዜም የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢኒስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው። እንደ ዶክተር ይፍሩ ገለጻ፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያስፈልጉና ወሳኝ ከሆኑት ግብአቶች እንደ ትራክተር፣ ማጨጃና መውቂያ የመሳሰሉ የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች ይጠቀሳሉ። በተጨማሪም በሰብልም ሆነ በእንስሳት ልማት የተሻሻለ ዝርያና አስፈላጊ ግብአቶች ያስፈልጋሉ። በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይልም ወሳኝ ነው። ሆኖም ግን የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እንዳይለወጥ (ትራንስፎርም) እንዳያደርግ ቀስፈው ከያዙት መካከል የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦት አለመኖር ነው። 90 በመቶ የሚሆነው የሰብል ልማት ሥራ የሚከናወነው በሬ በቀንበር ጠምዶ በማረስ ነው። ይህን ማነቆ ለመፍታት የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢኒስቲትዩት የግብርና ሜካናይዜሽንን ጥቅምና አስፈላጊነት በጥናት የተደገፈ አሳማኝ የሆነ ሰነድ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል በማቅረብ የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል። በዚህ የጥናት ሰነድ መንግሥትን ለማሳመን የተሞከረው ቀረጥ የተከፈለበትና ከቀረጥ ነጻ በግዥ ወደ አገር ውስጥ በሚገባ የግብርና ሜካናይዜሽን በሚሰጥ አገልግሎት መካከል ሊገኝ የሚችለውን ትርፍና ኪሳራ በሂሳብ ስሌት በማቅረብ ነው። ጥናቱ በምንግሥት አመኔታ አግኝቶ ከሶስት አመታት በፊት ጀምሮ የግብርና ሜካናይዜሽን ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ በመግባት ላይ ይገኛል፡፡

በተመቻቸው ነፃ ቀረጥ እድል የግብርና ሜካናይዜሽንን ተደራሽ ለማድረግ ክልሎች በስፋት ገዝተው ለማህበራት በማከፋፈል የግብርና ሜካናይዜሽንን ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እያደረጉ ሲሆን፣ በግላቸውም በመግዛት አገልግሎት የሚሰጡም ቁጥራቸው እየጨመረ ነው። እንደ አገር ባጋጠመው የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግርና በተለያዩ ምክንያቶች የግብርና ሜካናይዜሽን ዋጋ ውድ ነው። ይህም በተደራሽነትና በአገልግሎት ዋጋ ላይ ውስንነት ይፈጥራል። በተለይም ለአገልግሎት የሚጠየቀው ገንዘብ ከአቅም በላይ ሲሆን አርሶአደሩ ሊጎዳ ይችላል። ለዚህ መፍትሄው አርሶአደሩ በሚቀርብለት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን፣ ከሰብል ልማት በተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅበታል። አብዛኛው የኢትዮጵያ አርሶ አደር ከአንድ ሄክታር በታች (ሰባት ነጥብ ሰባት) የመሬት ይዞታ ነው ያለው። ተጨማሪ ገቢ ከሌለው ያለው የመሬት መጠንና አቅም ትራክተር ለመጠቀም አያስችለውም፡፡



ዶክተር ይፍሩ ታፈሰ



ዶክተር አበራ ደሬሳ

ሌላው መፍትሄ ኩታገጠም (ክላስተር) የግብርና ዘዴን መጠቀም ነው። መንግሥትም በአሁኑ ጊዜ በዚህ አቅጣጫ እየሰራ ይገኛል። አሁን ባለው አንድ ኩታገጠም (ክላስተር) 15 ሄክታር ነው። አርሶአደሩ በዚህ መንገድ ከተንቀሳቀሰ የግብርና ሜካናይዜሽን ለመጠቀም ያስችለዋል። ያዋጣዋልም። ይህ ዘዴም ወጭ ቆጣቢ በመሆኑ አርሶአደሩን ተጠቃሚ ያደርገዋል። የተደራሽነትንም ክፍተት ይሞላል። በዚህ መንገድ እየተበረታታ በመሆኑ የተፈለገውን በግብርና ሜካናይዜሽን መጠቀምን ማጎልበት ይቻላል፡፡

እንዲህ ባለው የተደራሽነትና ተጠቃሚነት አሰራር እንዲሁም መንግሥት በግብርናው ዘርፍ የያዘውን ሰፊ የልማት እቅድ በግብርና ሜካናይዜሽን የማከናወን ተግባር በምን ያህል ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ሊያሳካው እንደሚችልም ዶክተር ይፍሩ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ማብራሪያ፤ ከሶስት ዓመት በፊት በግብርና ሜካናይዜሽን ግብርናውን ለማሳለጥ እቅድ ነድፎ እንደነበር አስታውሰዋል። ይህም እኤአ በ2030 የተሻገረ ግብርናን ለማየት ታሳቢ በማድረግ ነው። ቅድመ እቅድ ለማሳካትም የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። የተቀመጠውን ግብ ለማሳካትም ስድስት ዓመት ነው የቀረው። በተለያየ አቅጣጫ በግብርና ሥራ ያለው ተነሳሽነት ከፍተኛ ነው። በተፈጠረው መነቃቃትም በበጋ ቆላ መስኖ ስንዴ ልማት ላይ ውጤት ተመዝግቧል። ወደ ትግበራ የገባው የሌማት ቱሩፋት ሥራ ሲደመር የግብርናውን ልማት ከፍ ስለሚያደርገው ቢያንስ መዋቅራዊ ሽግግር ላይ የደረሰ ግብርና ይኖራል የሚል እምነት አለ። ብዙ አምራች እንደሚፈጠርም ይጠበቃል፡፡

የግብርና ሽግግሩን ለማሳካት ከመንግሥት ድርሻ በተጨማሪ የተለያዩ አጋሮችን ተሳትፎ ይጠይቃል። የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት አቅርቦት የሚጠበቀው ከግሉ ዘርፍ በመሆኑ ይበረታታል። በዘመናዊ እርሻ ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶችም ያስፈልጋሉ፡፡

አርሶአደሩን በሬ ጠምዶ ከማረስ ስራው በማላቀቅ በግብርና ሜካናይዜሽን ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ከተቻለ በኋላ ወደ ኋላ እንዳይመለስ በቁጥጥርና ክትትል የመደገፍ ሥራ የመንግሥት ድርሻ እንደሆነም መዘንጋት የለበትም። በተለይም ከማን ምን ይጠበቃል የሚለው ሊሰመርበት ይገባል። ዶክተር ይፍሩ በዚህ ላይ በሰጡት ማብራሪያ፤ አርሶአደሩ ያለምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ምርት ማምረት እንደማይችል ሁሉ የግብርና ሜካናይዝሽንን ጥቅም ሲገነዘብና ተጠቃሚነቱ ከፍ ሲል ግዴታ አድርጎ ነው የሚቀበለው። ፍላጎቱ አቅርቦቱን ይገፋዋል ተብሎ ነው የሚታሰበው፡፡

አርሶአደሩንና የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪውን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ የሕግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ በኩል መንግሥት የግብርና ፖሊሲ ክለሳ ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛል። ተከልሶ ወደ ተግባር ይገባል ተብሎ የሚጠበቀው ፖሊሲ ችግሩን እንደሚፈታም ይጠበቃል። እየተከለሰ ስላለው የግብርና ፖሊሲም ዶክተር ይፍሩ በሰጡት መረጃ፤ የዛሬ 21 ዓመት በወጣ የግብርናና ገጠር ፖሊሲ ነበር ዘርፉ ሲመራ የቆየው። በቀደመው እና ሁን ላይ ባለው የግብርና ልማት ሥራ ብዙ ልዩነቶች ተፈጥረዋል። ይህንን ለማጣጣም እንዲሁም እኤአ በ2030 በግብርና ሊደረስበት የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ለረጅም በቆየ ፖሊሲ ለመተግበር ስለሚያስቸግር ፖሊሲውን መከለስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ፖሊሲውም በ10 መሠረታዊ መስኮች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ዋና ዋናዎቹም የግብርና ቴክኖሎጂ ግብአት፣ የፋይናንስ (ገንዘብ) አቅርቦት፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ፣ የውሃ አጠቃቀም፣ አቅም ግንባታ ናቸው። ይህንም ኃላፊነት ተቀብሎ እየሰራ ያለው የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢኒስቲትዩት እንደሆነና ፖሊሲው ፀድቆ በቅርብ ጊዜ ወደ ትግበራ እንደሚገባም ዶክተር ይፍሩ ገልጸዋል። ቀደም ሲል የነበረው በፌዴራልና በክልሎች መካከል የነበረው ተቀናጅቶና ተናብቦ አለመሥራት ችግርም በዚህ ጊዜ በመሻሻሉ ለግብርናው ሥራ መሳለጥ መልካም ነገሮች ተፈጥረዋል። በበጋ ቆላ መሥኖ ልማት የተከናወነው የቅንጅት ሥራ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል ብለዋል፡፡

በዚሁ ላይ ተጨማሪ ሙያዊ አስተያየታቸውን የሰጡን በግብርና ሙያ በማማከር ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ እንደሆነ የነገሩን ዶክተር አበራ ደሬሳ ናቸው፡ ፡በኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ የተጀመረው ልማትና በሌማት ቱሩፋት መርሃግብር ግብርናውን ከፍ ለማድረግ በመንግሥት የተያዘው እቅድ አስፈላጊነቱ አያነጋግርም ያሉት ዶክተር አበራ፤ እቅዱን ለማሳካት በግብርና ሜካናይዜሽን የታገዘ ሥራ መሥራት ግድ እንደሆነ ነው የገለጹት። አቅርቦቱንም በአገር ውስጥ የሚቻለውን በአገር ውስጥ በመሸፈን፣ በአገር ውስጥ የሌለውን ደግሞ ከቀረጥ ነጻ በማስገባት አገልገሎት ላይ የሚውልበትን መንገድ በማመቻቸት የተጀመረውን የልማት ሥራ በማጠናከር ማፋጠን እንደሚጠበቅ ነው ምክረ ሃሳብ የሰጡት፡፡

እንደ ዶክተር አበራ ገለጻ፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀም እንደየአካባቢው ሥነምህዳር የሚለያይና አብሮ መታየት ያለባቸው ሌሎች ነገሮች በመኖራቸው በግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀም የሚደረስበትን ጊዜ ከወዲሁ ለመተንበይ ያስቸግራል። እድገቱ በአገር የገንዘብ አቅምና የግብዓት አቅርቦት ላይም ይወሰናል። በበቂ ገንዘብ መደገፍ ከተቻለ ይፋጠናል፡፡ካልሆነ ግን የእድገት ሂደቱ አዝጋሚ መሆኑ አይቀርም። ይህም ሆኖ የግብርና ሜካናይዜሽን ለመጠቀም ያለው ፍላጎትና ተደራሽ ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረት አበረታች በመሆኑ ደረጃ በደረጃ የሚፈለገው ግብ ላይ መድረስ ይቻላል። የግብርናው እድገት አበረታች በሚባል ደረጃ ላይ እንደሚገኝና አሁን መንግሥት በያዘው አቅጣጫም ተስፋ ሰጪ የሆነ ነገር መኖሩን ነው እንደዘርፉ ባለሙያ የታዘቡት፡፡

እርሳቸውን ጨምሮ በዘርፉ ላይ የሚገኙ የዘርፉ ባለሙያዎች የግብርና ትራንስፎርሜሽን አስፈላጊነት በተለያየ አጋጣሚ እና መንግሥትም በዘርፉ ምክር ፈልጎ ሲጠይቃቸው እያገዙ እንደሆነ የጠቆሙት ዶክተር አበራ። የምክር አገልግሎቱም የመንግሥትን የግብርና ፖሊሲና አቅጣጫ በመረዳት መሆን እንዳለበት፣ ይህን መሠረት አድርጎ የምክር አገልግሎት ሲሰጥም መንግሥት በዘርፉ ያወጣው ፖሊሲና ፕሮግራም አስፈላጊ ነው ወይንም አይደለም የሚል መከራከሪያ ለማቅረብ የሚያስችል አቅም ከአማካሪው የሚጠበቁ ተግባራት እንደሆኑም አስረድተዋል፡፡

የማማከሩ ተልእኮ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ወይንም እንዲያድግ ብቻ ሳይሆን የተመረተው ምርት ገበያ ላይ ውሎ በአርሶአደሩ ሕይወት ላይ ለውጥ ማምጣት የሚችልበትን መንገድ እንዲሁም ፣ ኢንዱስትሪውንም የሚመግብና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውን በሚያጎላ መልኩ የሚቀመጡ አቅጣጫዎችን ማመላከት መሆን ይኖርበታል ብለዋል፡፡

የማማከር አገልግሎቱ ሙያን መሠረት ያደረገ ሲሆን ውጤቱም እንደሚያመረቃ ገልጸዋል። መንግሥትም የአማካሪዎችን ሙያዊ ድጋፍ ለመቀበል ዝግጁ ካልሆነ ማማከሩ ትርጉም እንደሚያጣ ነው የተናገሩት። መንግሥት የሙያ ምክሩን ካልተገበረ ችግሩ ከአማካሪዎች ወይንም የመንግሥት ተደርጎ እንደሚወሰድም ነው ያስረዱት። አማካሪና መንግሥት ተናብበው ከሰሩ ግን ውጤት ይገኛል የሚል እምነት አላቸው። ‹‹ግብርናው አዝጋሚ ሆኖ ሳይሆን በፍጥነትና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ነው እድገት ማስመዝገብ ያለበት፡፡አሁን ካለው በእጥፍ መመረት ይኖርበታል። ይህ ሲሆን ነው ለውጥ መጣ የሚባለው›› ሲሉም አክለዋል፡፡

ዶክተር አበራ እንደአአገር የመንግሥት የገንዘብ አቅም ውስንና ያለው የገንዘብ አቅምም ለተለያዩ የልማት ዘርፎች የሚውል ቢሆንም ግብርናው ላይ ግን የተለየ ትኩረት መሠጠት አለበት የሚል አቋም አላቸው። አሁን ላይ ለግብርናው ዘርፍ በመንግሥት እየተበጀተ ያለው በጀት ግብርናውን በፍጥነት ለማሳደግ የሚያስችል ነው የሚል እምነት የላቸውም። ለዘርፉ በቂ ፋይናንስ መመደብ አለበት ከሚሉ ወጎኖች መካከል ናቸው። ለዘርፉ የተሻለ የገንዘብ ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ በበጋ ቆላ መስኖ ስንዴ ልማት የታየው የተናበበ እቅድና ክንውን በሌሎችም እንዲደገም ማድረግ እንደሚገባም ምክረ ሃሳብ ሰጥተዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ‹‹ውጤቱ የአገርን የትምህርት ደረጃ ያሳየ በመሆኑ ሁሉም ሊማርበት ይገባል››

## - ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎቻቸውን ያሳለፉ ትምህርት ቤቶች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

‹‹የ12ኛ ክፍል አገራዊ ውጤት ምርቱን ከገለባ የለየ ነው። በተለይም የሚሰሩ ተቋማትን ትጋትና የተማሪዎቻቸውን ጥረት አሳይቷል። የአቅም ውስንነታችን ምን ላይ እንደሆነም ያመላከተ ነበር። የት የት አካባቢ በስፋት መስራት እንደሚያስፈልግም ጠቁሟል። የትምህርት ቤቶች የማስተማር ብቃትን ለይቷል። ምክንያቱም ከዚህ በፊት በነበረው አሰራር ሙሉ ማሳለፍ እንጂ ጥራት የሚባል ነገር ለውድድር አይቀርብም። በዚህም ዩኒቨርሲቲ የሚገባው ጎበዙ ብቻ ሳይሆን በቂ እውቀት ያልጨበጡትም እንዲሆኑ አድርጓል። ምክንያቱም የመግቢያ ነጥቡ በኩረጃና መሰል ተገቢ ያልሆኑ ስራዎች ጋሽቧል። ስለዚህም ሰነፉ የጎበዙን ጭምር እድል ዘግቶበት ቆይቷል። በዘንድሮው ውጤት ይህ የተቀየረ ይመስላል›› ያነጋገርናቸው ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎቻቸውን ያሳለፉ ትምህርት ቤቶች ሃሳብ ነው።

እንደ አገር ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበውንና ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎቹን ያሳለፈውን መነሻ ስናደርግ የይሁኔ ወልዱ መታሰቢያ ደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ሲሆን፤ የትምህርት ቤቱ የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተናን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስፈተነ ነው። የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች መግቢያ ዝቅተኛው 350 ቢሆንም የአዳሪ ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ያመጡት ዝቅተኛው ውጤት 450 ነው። ከፍተኛው እንደአገር የተመዘገበው 666 ነውም። ለውጤቱ የተማሪዎች ትጋት የመጀመሪያ ሲሆን፤ የመምህራን መረጣና ሥራቸው ታክሎበት ስኬታማ አድርጓል።

የትምህርትቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ በለጠ ኃይሌ እንዳሉት፤ ቀጠናው የጦርነት በመሆኑ ምክንያት ለስድስት ወር ያህል ተማሪዎቹ መማር አልቻሉም ነበር። በኮሮና ምክንያትም እንዲሁ ግማሹን ሴሚስተር አልተማሩም። ትምህርትቤቱ ጥቃት ከደረሰባቸው መካከልም ነው። ሆኖም በልመና ግብዓቶችን አሟልተን ተማሪዎችን አስፈትነናቸዋል። እንደ አዳሪ ትምህርት ቤት ሳይሆን እንደ ሁለተኛ ደረጃ ነው የግብዓቱ ጉዳይም። ነገር ግን ሁሉንም በመቻል ለዚህ በቅተዋል።

በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ የሚተዳደረው የቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሸርድ ካምፓስ ፕሪንሲፓል የሆኑት አቶ አቤል ጫላ እንደሚሉት፤ ትምህርት ቤቱ ከዚህ በፊት በነበረው የአፈታተን ሥርዓት ተማሪዎችን ዩኒቨርሲቲ ሳያስገባ ቀርቶ አያውቅም። በየዓመቱ የተሻለ ተማሪ እንጂ ዝቅተኛ አቅም ያለው ተማሪም አያወጣም። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የመማር ማስተማር ሥራውን በሚገባ ማከናወን መቻሉ ነው። ከዚያ ባሻገር ተማሪዎቹ ለውጤት ሳይሆን ለእውቀት የሚሰሩ መሆናቸው፣ ዓላማ ያላቸውና ለዚያ ስኬት የሚተጉ መሆናቸው ውጤታማ አድርጓቸዋል። በተመሳሳይ ምንም እንኳን መምህራኑ የተመረጡና ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሌክተሮች ቢሆኑም ተማሪው ጠንካራ ካልሆነ የሚያሰሩበት እድል አይገጥምምና ይህም መልካም እድሎችን ሰጥቷል።

ተማሪዎችን ከመፈተናችን በፊት ሁሌም የተለየ ልምድ የማጋራት ሥራ ይሰራል። በተለይም ከፈተና ጋር በተያያዘ ተረጋግተው እንዲፈተኑ ከማድረግ አኳያ የማያሰልስ ጥረት ይደረጋል። በተለይም በዘንድሮው ዓመት ልዩ ክትትልና ዝግጅት ተደርጎ ነው ወደፈተናው የገቡት። ምክንያቱም አዲስ የፈተና ሥርዓት ተፈጥሯልና ጎበዝ ቢሆኑም የሥነልቦና ጫና ሊፈጥርባቸው ይችላል። ስለዚህም ዩኒቨርሲቲው ያለውን ልምድ በፕሬዚዳንቱ ዶክተር ብርሃነ መስቀል ጠና በኩል ከማጋራት ባሻገር የፈተና የሥነልቦና ዝግጅት ሥልጠና እንዲወስዱ አድርጓል። በዚህም ተስፋ የተጣለባቸውን ያህል ሰርተው እንዲያሳዩ ሆነዋል።

የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሸርድ ካምፓስ በየዓመቱ 90 ተማሪዎችን የሚቀበል ሲሆን፤ በኮቪድ ወቅት ብቻ በክፍል ውስጥ የሚማሩትን ተማሪዎች ለመቀነስ ሲል 75 አድርጎ ነበር። የአቀባበል ሁኔታው የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የ8ኛ ክፍል ክልል አቀፍ የፈተና ውጤት ሲለቅ ከፍተኛ ውጤቱን መሰረት በማድረግ ነው። የመቀበል ሁኔታው በ12 የማማሪያ ክፍሎች በላይ የሚሸፍን ስላልሆነ ከትምህርት ቤቱ በጣም ርቀው ያሉ ተማሪዎች በትራንስፖርት ምክንያት፣ ሀብታም ከሚባል ቤተሰብ የወጡ ልጆች ትምህርት ቤቱን ላይመርጡ ይችላሉና ለውድድር እስከ 5ሺ ተማሪዎች ግምት ውስጥ እንዲገቡ ተደርጎ ምዝገባው ይካሄዳል።

የትምህርት ቤት መግቢያ ፈተናው ሲሰጥ የስምንተኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ውጤት ከ 15 በመቶ ማርክ አይበልጥም። ምክንያቱም ውጤቱ በኩረጃና መሰል መንገዶች ሊመጡ ይችላሉ። ስለዚህም ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች ለመለየት ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ፣ ሂሳብ፣ ፊዚክስ እና አፕቲቲዩድን የያዘ ጥራቱን የጠበቀ ፈተና ይወጣል። መምህራኑም ፈተናውን እንዲያርሙ የሚደረገው በሚስጥር ቁጥር (ኮድ) ነው። ስለዚህ እያንዳንዳቸው ትምህርቶች 15 በመቶ ማርክ እንዲይዙ ተደርገው ከስምንተኛ ክፍል (ሚኒስትሪ) ውጤት ጋር በመደመር በጥቅሉ 90 በመቶ ላይ ይደርሳል። የቀረው 10 በመቶ ደግሞ ከፈጠራ ስራ፣ ከሳይንስ ዝባሌና ከቴክኖሎጂ ጋር የተገናኙ ጥያቄዎች ቦታ ተሰጥቷቸው ከዩኒቨርሲቲው የተውጣጡ ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች ቃለመጠይቅ እንዲያደርጉላቸው በማድረግ ይፈተናሉ። ይህ የሚሆነው በትምህርት ቤቶቹ ለመግባት በቂ ውድድር መደረግ ስላለበት ነው። በፈጠራ ሥራቸው በየጊዜው የተሻሉ ነገሮችን ለአገር ማበርከት ስለሚጠበቅባቸው ነው። ከዚህ ባሻገር በዩኒቨርሲቲና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የውጭ አገር የትምህርት እድል እንዲያገኙ ለማስቻል ታስቦ እየተሰራ ነው። ስለሆነም ይህንን ለማሳካት የጠራ ተማሪ ማስገባት ያስፈልጋልና ምልመላው በዚህ መልኩ ይደረጋል ይላሉ ፕሪኒስፓሉ።

ሥራው የተጀመረው ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ እና ከአራዳ ክፍለ ከተማ ጋር በጥምረት ቢሆንም የትምህርት ቤቱን ወጪ መቶ በመቶ የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከራሱ ባጀት ላይ ቀንሶ በመሆኑ ትምህርት ቤቱ የአንድ አካል ሳይሆን የመንግሥት ነው። በዚህ መልኩ ጠንክሮ ተማሪዎችን ለውጤት ማብቃቱ በአንድም በሌላም መንገድ ኢትዮጵያን ሊጠቅሙ የሚችሉ ተማሪዎችን የማፍራት አንድ አካለ ነው። ትምህርት ቤቱ ሁሉንም ተማሪ ሳይንቲስት ማድረግ በሚል መርህም እየሰራ ነው።

ትምህርት ቤቱ የ12ተኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተናን ለአራተኛ ጊዜ ሲያስፈትንም ይህን እያሰበ እንደሆነም ሃላፊው ያነሳሉ። እንደ አገር ለተከታታይ ዓመታት ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ተችሏል። ነገር ግን ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤትን ለምን አላመጡም የሚለው ያነጋግራል። ምክንያቱም የገቡት በከፍተኛ ጥራት ውስጥ አልፈው ነው። ስለዚህም ልኬቱ ይህ ስለሆነ ሙሉ ለሙሉ ማለፋቸው አይደንቅም። በ12ኛ ክፍል ብቻ ሳይሆን በ10ኛ ክፍልም የሚታይ ተግባር ነው። በሌላ በኩልም እነዚህ ተማሪዎች አልፎ ተርፎ የዓለም አቀፍ ፈተና እንዲወስዱ እየተደረገ ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ይመለከታሉ። በዚህም ውጤታማ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

ስለዚህም በዘንድሮው ዓመት ብቻ የ 12 ክፍል መልቀቂያ (ማትሪክ) ሳይወስዱ የውጭ የትምህርት እድል አግኝተው በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች የገቡ ተማሪዎችን ማፍራት ችለናል። በዚህም የአሁኑን ፈተና የወሰዱት 69 ተማሪዎች ሆነዋል። ከእነዚህ ውስጥም 16 ተማሪዎች ከ600 በላይ፤ 32 ተማሪዎች ከ500 በላይ፤ 20 ተማሪዎች ከ400 በላይ ፤ 1 ተማሪ 375 ማምጣት ችሏል። ለዚህ ውጤት ስኬት የመጀመሪያውን ድርሻ የሚወስደው የተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት ሲሆን፣ መሆን የሚፈልጉትን አውቀው የሚሰሩ ስለሆኑ ለዚያ ግብም የሚሰሩ ናቸው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የመምህራን የመዘጋጀት ከፍታ፣ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች ለትምህርት ቤቱ ልዩ ትኩረት መስጠታቸው የእነርሱ ጥረት መታከል ውጤቱን የሚጠበቀው ላይ አድርሶታል።

አሁን የተጀመረው የመንግሥት ግልጸኝነት ብዙ ነገሮችን በቀጣይ የሚቀንስ እንደሆነ የሚያነሱት አቶ አቤል፤ ይሰረቅ ይሆን የሚለውን የጎበዝ ተማሪዎች ስጋት በብዙ መልኩ ገቶታል። የተማሪዎችን የሥራ ውጤትም አሳይቷል። በተመሳሳይ ይህ ውጤት የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ከታች የነበረውን ድክመት እንደሆነም አመላክቷል። ስለዚህም እንደ እኛ አይነት ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎቻቸውን ቢያሳልፉም የሌሎቹ ትምህርት ቤት ጉዳይም ያሳስባልና በዚያ ላይ መስራት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።



**አቶ አቤል ጫላ**



**አቶ ግርማ ደነቀ**

በአሁኑ ፈተና ከፍተኛ ወጪ ወጥቶ ሊሆን ይችላል። ሆኖም የቀጣይ ተስፋን የሚያለመልምና የትምህርት ሥርዓቱን ስብራት የሚያክም ስለሚሆን ሁሉም ደስተኛ ሊሆንበት ይገባል። የአፈታተን ሥርዓቱም የአንድ ጊዜ ሥራ ስላልሆነ ሁሉም መረባረብ አለበት። ምክንያቱም ዘመቻው ትውልድ የመፍጠር ጉዳይ በመሆኑ ፤ ስለዚህ ስህተትን አይቶ፣ ችግርን ፈትቶ የተሻለ ተማሪ ለመፍጠር በጋራ መስራት ያስፈልጋል። በተለይም ምንም ያላሳለፉት ላይ ምክንያታቸውን እያዩ ማገዝ ይገባል። በተጨማሪም እንደመንግሥት አሁን ያለውን አቋም ማስቀጠል፤ ተማሪዎች በራሳቸው የመስራት ልምምዳቸው በዚህ እንዲቀጠል ማድረግ ይኖርባቸዋል ሲሉ አስተያየታቸው ሰጥተዋል።

የወላይታ ሊቃ አዳሪ ትምህርት ቤት ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ግርማ ደነቀ በበኩላቸው ፤ የትምህርት አሰጣጡንና የአሁኑ አገር አቀፍ የ12ኛ ክፍል ፈተና ውጤት በተለያየ መንገድ እያነሱ ያብራራሉ። ትምህርት ቤታቸው የተለዩና አቅም ያላቸውን ተማሪዎች ማፍራትና ማሳለፍ የጀመረው ዛሬ ሳይሆን ከተቋቋመበት 2000 ዓ.ም ጀምሮ ነው። አቀባበላቸው ከአምስተኛ እስከ ሰባተኛ ክፍል ድረስ የሚማሩ ተማሪዎችን ሲሆን የቀደመውን የትምህርት ደረጃ ምን ያህል አውቀውታል መለያቸው ነው ፤ ስምንተኛ ክፍል ላይ ሌላ ተጨማሪ ተማሪ በፈተና ለይተው ይቀበላሉ።

ከ75 በላይ አማካኝ ውጤት እያስመዘገበ መቀጠል የማይችል ተማሪ በትምህርት ቤቱ እንዲቆይ አይደረግም። ስለዚህም ውድድሩ ከውጪ ካሉት ጋር ብቻ ሳይሆን ከውስጥ ካሉት ጋርም እንደሆነ ያነሳሉ። ምክንያቱም በትምህርት ቤቱ ውስጥ የመቆየትና ያለመቆየት ጉዳይ ስላለበት። ውጤታማ ተማሪ ለመሆን ሌት ተቀን ያጠናሉ። መምህራንን ሞጋችና ሳያውቁ የማያልፉ ናቸው። ተወዳዳሪነታቸው በአገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ጭምር የሆነውም በዚህ ምክንያት ነው። አዲስ ነገር ሲፈጠርም ያልወደቁት በራስ መሥራትን እየተለማመዱ በመሄዳቸው ነው።

ከ2005 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ 721 ተማሪዎችን ያስፈተኑ ሲሆን፤ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎችን በተለያየ ደረጃ ተቀላቅለዋል። ስለዚህም ዩኒቨርሲቲ ማስገባት ዘንድሮ የተጀመረ አይደለም። ይህንን ልዩ የሚያደርገው ትምህርት ሚኒስቴር የፈተና አሰጣጡን ለየት ማድረጉ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች በራሳቸው አቅም ምን ያህል ይሰራሉ የሚለውን የፈተሸ በመሆኑ የእኛም ተማሪዎች ይህን አልፈው ዩኒቨርሲቲ ሙሉ ለሙሉ እንዲገቡ ሆነዋል። በእርግጥ ያስፈተናናቸው ተማሪዎች ከሌሎች አኳያ ሲታይ ቁጥራቸው ትንሽ ነው። በዘንድሮው ዓመት የተፈተኑት 75 ተማሪዎች ብቻ ናቸው። እነርሱም 300 ቤት ያመጡት ሁለት ብቻ ሲሆኑ፤ ከ400 እስከ 499 ያመጡ ደግሞ 28 ናቸው። 500 እና ከዚያ በላይ ያመጡት ደግሞ 41 ሆነው ተገኝተዋል።

በአንድ ክፍል የተማሪ ቁጥር በዛ ቢባል 38 ሲሆን፤ ይህ ደግሞ መምህራንና ተማሪዎች ተቀራርበው እንዲሰሩ አስችሏል። በወላይታ ልማት ማህበር መደገፉና አስፈላጊ ነገሮች መሟላታቸው እንዲሁም የአሰራር ሥርዓቱ ተወዳዳሪ የሚያደርግ መሆኑ ለተማሪዎች ውጤት ከፍ ማለት አስተዋጽኦ ነበረው። ትምህርት ቤቱ በዚህን ያህል ልክ ውጤታማ ስራን ይስራ እንጂ የአጥር ግቢው በደንብ የታጠረ ባለመሆኑ አንዳንድ ችግሮች ያጋጥሙታል። በዚህ ላይ መንግሥት ቢያግዝ የበለጠ ለመሥራት ያስችላል ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

የተማሪዎች ውጤትን ከፍ ለማድረግ የመጀመሪያ የሚሆነው ዓላማ ያለው ተማሪ መፍጠር ነው። በተለይም በሥነ ምግባር ማነጽ ከተቻለ በራሱ ሰርቶ የማለፍና ለሌሎች የሚያሳልፍ ዜጋ መፍጠር ይቻላል። አሁን ያለው የትምህርት ጥራት ጉዳይም በዚያው ልክ እየተረጋገጠ እንዲሄድ መስመር ያስይዛል። እናም በዘንድሮው የውጤት አተናተንና የማለፍ ምጣኔ ሁሉም መደሰት አለበት። ምክንያቱም ተማሪ ስለወደቀ ሳይሆን ለአገር የሚሆን ተስፋ መሰረት ስለተጣለ።

እስከዛሬ በነበረው ተግባር የትምህርት ጥራት እንደአገር አደጋ ውስጥ ገብቷል ይባላል። ሆኖም መፍትሄ ሰጪ አካል አልነበረም። መንግሥት ጭምር ኃላፊነቶችን መውሰድ አይፈልግም ነበር እኛንና እኛን የሚመስሉ ትምህርትቤቶች ላይ ጭምር ይህ አካሂድ አደጋ ፈጥሮ ነበር። ምክንያቱም ለፍተን እንዳለፉን ሲያደርገን ቆይቷል። 24 ሰዓት ሲያነብና ለተሻለ ነገር ሲጥር የነበረውን ልጅ እድል አሳጥቶታልም። ይህ ደግሞ ተመርቆ ሥራ ላይ የተሰማራውን ሰው ጭምር እንዲበላሽ አድርጎታል። የማንመከተው ነገር እንደ ▯ገር የገጠመንም በዚህ ምክንያት ነው የሚሉት አቶ ግርማ፤ ዛሬ ግን ነገር ተቀይሯል። ትውልድ በመግደል ላይ የተስማማው ዛሬ በኔ ይብቃ ማለት ጀምሯል። መንግሥት ራሱን ግልጽ ከማድረግ ጀምሮ ያሉትን ችግር አሳይቷል። መፍትሄው ምን እንደሆነም አመላክቷል ብለዋል።

ትምህርት አሁን ላይ ቀጥተኛ የሆነ ለውጥ ያስፈልገዋል። ምክንያቱም ትውልድን በብዙ መልኩ ሳንገራው አልፏል። አሁን ግን የእስካሁኑ ይብቃ ሌሎች ይዳኑ በማለት ለውጡን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማፋጠን ተገቢ ነው። በተለይም ትምህርት ሚኒስቴር አሁን እየሄደበት ያለውን ጉዞ ማጠናከር አለበት። ሌሎች ከትምህርት ተቋማት ውጪ ያሉ ሊያግዙት ይገባል። ምርጫም ቢሆን የሚደረገው ጥራትና ብቃት ታይቶ ነው። እናም ለመመረጥ ብቁ መሆን ግዴታ ነው። ለዚህ ደግሞ በብቃት መማር ያስፈልጋል። እውቀት ግድ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

ሰባት ትምህርት ቤቶች ብቻ ሰርተው አገርን ሊያስቀጥሉ አይችሉም። የዘንድሮ የፈተና ውጤት እንደአገር ሲታይ ኪሳራው በኢኮኖሚም፣ በማህበራዊም ሆነ በፖለቲካውም ዘርፍ ነው። ስለሆነም በአገር ደረጃ ተረባርቦ መድሃኒት መፈለግ ያስፈልጋል። ስለዚህም ምንም ያላሳለፉ ትምህርት ቤቶችን ማንሳት ላይ መስራት ይገባል። ተሞክሮ ከማጋራት ባለፈ የሚደግፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት የግድ ነው።

ውጤቱ እንደአገር ያለንበትን ሁኔታ አሳይቶናል። በተመሳሳይ የእርስ በእርስ መረዳዳቱ ላይ እንድንተጋም ያደርገናል። ስለሆነም ምንም ተማሪ ያላሳለፉ ትምህርት ቤቶች ማድረግ ያለባቸው ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ከችግራቸው መማርና ለመፍትሄው መስራት ነው።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹መንግሥት በቁርጠኝነት ከዲያስፖራው ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ማሰቡ የሚያስመሰግነው ነው››

**አቶ አለባቸው ደሳለኝ**
**የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት**
**የውጭ ግንኙነት ዘርፍ የእቅድና ፕሮግራም ኃላፊ**

ማህሌት አብዱል

ነዋሪነታቸው በእንግሊዝ ለንደን ከተማ ነው። ከ 28 ዓመታት በላይ በስደት ኖረዋል ፤ በእነዚህ ዓመታት በተለያዩ መንገዶች በውጭ ዜጎች እጅ የገቡ የኢትዮጵያ ቅርሶችን በከፍተኛ ዋጋ በመግዛትና በማሰባሰብ ይታወቃሉ። በቀድመው መንግሥት ተገፍተው ለስደት የተዳረጉ ቢሆንም የሀገራቸውን መልካም ገፅታ ለመገንባት ቦዝነው አያውቁም። ከዚህም አልፈው እንደእርሳቸው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ቅን አሳቢ ኢትዮጵያውኖችን በማሰባሰብ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግም የራሳቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ለለውጡ መምጣት በውጭ ሆነው ሲታገሉ ከነበሩ ሰዎችም አንዱ ናቸው፤ ለውጡ ከመጣ በኋላም የሀገራቸው አምባሳደር በመሆን በውጭ የሚደረገውን ተፅዕኖ በመከላከል ረገድ የላቀ ሥራ ሰርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ የተግባር ምክር ቤት እንዲመሰረት ዋነኛ ሚና ተጫውታዋል ፤ ለዘመናት በስደት የኖሩ ዲያስፖራዎችን በማስተባበር በጦርነት የቆሰሉ የሠራዊቱ አባላትን፤ ዜጎችን በመደገፍ፤ የፈረሱ ቤቶችንና ከተሞችን በመገንባት ረገድም ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል፤ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ይህንን አስዋፅኦቸውን የተመለከተው መንግሥትም በቅርቡ €€ኢትዮጵያ ታመሰግናለች« ብሎ በሰየመው የእውቅና እና የምስጋና መርሃ-ግብር ላይ ከሸለማቸውና እውቅና ከሰጣቸው መካከል አንዱ ናቸው ፤ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት ዘርፍ የእቅድና ፕሮግራም ኃላፊ አቶ አለባቸው ደሳለኝ ደሳለኝ ።

እኛም ከአቶ አለባቸው ጋር በእውቅና መርሃ-ግብሩና በሌሎችም ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አድርገን ፤ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡



ፎቶ፡-ኤጋጊ ገዮን

**አዲስ ዘመን፡-በቅድሚያ እንኳን ደስ አልዎት፤ እስካዛሬ ለሀገር ላደረጉት አስተዋፅኦ በመንግሥት የተሰጥዎት እውቅና እና ምስጋና ምን አይነት ስሜት ፈጠረብዎት ?**

**አቶ አለባቸው፡-** በመሰረቱ መልካም ስራ መስራት መልካም ቢሆንም በመንግሥት ደረጃ ምስጋና እና እውቅና መስጠት የተለመደ አይደለም። መንግሥት ብዙ ሳይዘገይ እንደዚህ አይነት ነገሮች ማድረጉ ጠቃሚ ነው ባይ ነኝ። በተለይም የኢትዮጵያ መንግሥት አስቦበት ከዲያስፖራው ጋር ያለውን የተቀራረበ መልካም ግንኙነት ለማጠናከር የወሰዳቸውን እርምጃዎች የዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት በአድናቆት ይመለከተዋል ።

በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ የራሱ ጥናቶች ካደረገ በኋላ በተለያዩ ማህበራት የተደራጁ ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ያደረጓቸውን አስተዋፅኦዎች በመመልከት ኢትዮጵያ ታመሰግናለች በሚል መሪ ሃሳብ ጥሪ የደረሰኝ ቢሆንም ጥረታችን እንደግለሰብ ብቻ ባለመሆኑ ምክር ቤታችንም አምኖበት ነው ወደዚህ የላከኝ።

ከሁሉ በላይ መገንዘብ የሚገባው ጉዳይ በመንግሥት የተሰጠን ምስጋና እና እውቅና ብቻ ሳይሆን አደራም ጭምር መሆኑን ነው። ከዚህ እንደሄድን ከቀድሞው በላቀ ሁኔታ የሀገራችን መልካም ገፅታ በውጭው ዓለም የመገንባትና ትውልዱን የመቅረፅ ሃላፊነት አለብን። አሁን እውቅና የተሰጠን ሰዎች፤ የእዚህ ውጤት ተካፋዮች እኛ ብቻ አይደለንም፤ በመላው ዓለም ያለው ከሶስት ሚሊዮን የሚልቁ ዲያስፖራዎች ጭምር ናቸው ። በመሆኑም ለእኔ እውቅናው ይህንን የሕዝብ ሃላፊነት ይዘን እንድንመለስ ማሳሰቢያም ጭምር ነው ባይ ነኝ።

እውቅና መሰጠቱ በዲያስፖራው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሞራል መነቃቃትን ይፈጥራል፤ በቀጣይም በላቀ መንፈስ ለሀገሩ ዘብ እንዲቆም ጉልበት ይሆነዋል። ደግሞም በስደት ሀገር ሆነን ለምንሰራው ስራ ለካስ ተመልካች አለ፤ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚያሳስበው አካል አለ፤ ብለን እንድናስብ አድርጎናል፡፡

በመሰረቱ መንግሥት ‹‹እናመሰግናለን›› ብሎ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሽልማት ሲሰጥ መልዕክቱ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ያለበትን የጋራ ሃላፊነት እና ብሔራዊ ግዴታውን እንዲወጣ የሚያነሳሳ መልዕክት ነው ። ከዚህ አንጻር መንግሥት ከዲያስፖራው ጋር ያለውን ግኑኝነት ለማጠናከር በቁርጠኝነት ለመስራት ማሰቡ የሚያስመሰግነው ነው።

በተለይም ደግሞ ባለፉት ዘመናት የነበሩ አንዳንድ አለመግባባቶችና ኩርፊያዎችን ለመፍታት መንገድ ይከፍታል ብዬ አምናለሁ። ዋናውና ትልቁ ነገር በሀገር ላይ ማኩረፍ እንደማይቻል፤ ተቻችሎ መኖር እንዳለብን በመገንዘብ የበለጠ ለመስራት ያስችለናል። በአጠቃላይ እውቅናው እና ምስጋናው በቀጣይ ዲያስፖራው መስራት በሚገባው ጉዳዮች ላይ ሃላፊነቱን እንዲወጣ መልእክት እንድናደርስ የተሰጠን እንጂ የየግላችንን ዝና ለመገንባት እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ምክርቤታችሁ በተለይ ባለፉት አራት ዓመታት ለሀገር ከሰራው ስራ አንጻር እውቅናው የሚገባው ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ አለባቸው፡-** በቅድሚያ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ እኛ እስከዛሬ ለሀገርና ለሕዝብ ድጋፍ ስናደርግ የነበረው ለሽልማት ወይም ለምስጋና ብለን አይደለም ። ይልቁንም እንደ አንድ ዜጋ ለሀገር ማበርከት የሚገባንና ያልከፈልነው እዳ መኖሩን ስለምንናምን ነው። በዋናነትም ብዙ ዋጋ ከፍሎ ላሳደገን፤ ላስተማረንና እዚህ ላደረሰን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ መሆን ስለሚገባን ነው። ይህንንም ታሳቢ በማድረግ ኢትዮጵያ በተጎዳችበትና አደጋ ላይ በወደቀችበት ወቅት ሁሉ ከጓኗ ሆነን የበኩላችንን ጥረት አድርገናል።

በተለይም ከአንድ ዓመት በፊት በህልውና ዘመቻው ከሕዝብና ከመንግሥት ጎን ሆነን አጋርነታችንን አረጋግጠናል። ከማንም በፊት ቀድመን በጦርነቱ የፈራረሱ ቤቶችን በመጠገን፤ የተጎዱ የሠራዊት አባላትን ለመደገፍ ከአሮውፓም ሆነ ከሌሎች የዓለም ጫፎች ተሰባስበን ሀገራችን ድረስ በመምጣት ደማችንን ለግሰናል፤ የተሰባሰበውን እርዳታም ለግሰናል። በመቀጠልም የአባይን ግድብ ሄደን በማየት የደረሰበትን ደረጃ ፈትሸን ለግድቡ የሚሆኑ አስፈላጊ ድጋፎችን አድርገናል።

የመጣነው በመስከረም ወር ላይ በመሆኑ እንቁጣጣሽ ኢትዮጵያ በሚለው መርሃችን ውስጥ እነዚህ ኢትዮጵያን ደን ለማልበስ ይደረግ በነበረው በአረንጓዴው ዘመቻ እኛም አሻራችንን አስቀምጠናል። ከሞላ ጎደል 80 በመቶ የሚሆነው እቅዳችንን አሳክተን ተመልሰናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ምክር ቤታችሁ በሀገር ጉዳይ ላይ በዋናነት ትኩረት አድርጎ የሚሰራቸው ስራዎች ምንድን ናቸው?**

**አቶ አለባቸው፡-** በዋናነት የምንቀሳቀሰው ሶስት ዓላማዎችን ይዘን ነው ፤ በመጀመሪያ በመላው ዓለም የኢትዮጵያን መልካም ገፅታ መገንባት ፤ በዚህም በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሀገራችን የዓለም ምርጥ የቱሪዝም መዳረሻ ትሆን ዘንድ ዲያስፖራው በእረፍት ጊዜው ሌሎች ቦታዎች ከመሄድ ይልቅ ሀገሩን እንዲጎበኝ ቅስቀሳ እናደርጋለን።

በነገራችን ላይ በርካታ ዲያስፖራዎች ሀገራቸውን በሚገባ አያውቋትም፤ ጥቂት የማይባሉት ልክ እንደምዕራባውያኑ ኢትዮጵያን የሚያውቋት በችግር እና ጦርነት ብቻ ነው። በመሆኑም ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ የሚደረገው ቅስቀሳና አላስፈላጊ የሆነ ጸረ ኢትዮጵያ አቋምም ለመስበር ትልቅ ስራ እንሰራለን።

ሁለተኛው አቅሙና እውቀቱ ያላቸው ዲያስፖራዎችም ሆነ የውጭ ሀገር ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ የማበረታት ስራ እንሰራለን። በሶስተኛ ደረጃ የምንሰራው ትውልድ ቀረፃ ላይ ነው። የትውልድ ቀረፃ ስንል ደግሞ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ለኢትዮጵያ ቀጣይነት ወሳኝ በመሆኑ ወጣቱ በባህል፤ በታሪክ እንዲሁም ደግሞ በትምህርት ፖሊሲ ላይ እንዲሳተፍ እንዲተባበርና በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ያገባኛል የሚል ፍላጎት እንዲኖር ማስቻል ነው። በነዚህ ጉዳዮች ትልቁን ሃላፊነት በመውሰድ እየሰራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ህብረቱን አጠናክሮ መስራቱ በሀገር ላይ ምን በጎ አስተዋፅኦ አበርክቷል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ አለባቸው፡-** እንደሚታወቀው በቀደሙት ዓመታት ዲያስፖራው በተለያዩ ምክንያቶች የኖረው ተከፋፍሎ ነው። ፖለቲከኞቹ ለራሳቸው ፍላጎት ሲሉ የሚወስዷቸው ያልተገቡ ቅስቀሳዎች ስለነበሩ አንድ ለመሆን ተቸግሮ ነበር። በተለይም ደግሞ የማህራዊ ሚዲያ አክቲቪስቶች ራሳቸውን ለመሸጥና ተከታዮቻቸውን ለማብዛት ሲሉ ያደርጉት የነበረው ሁኔታ ዲያስፖራውን ከፋፍሎት ነበር።

ለውጡ ከመጣ በኋላ ግን ዲያስፖራው ወደ አንድነትና ወደ ኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ መምጣት ጀምሯል። በተለይም ደግሞ ዶክተር ዐቢይ ያደርጉት የነበረው የኢትዮጵያዊነት ቅስቀሳ በእያንዳንዱ ዲያስፖራ ውስጥ ከፍተኛ መነሳሳት ፈጥረዋል። አንድነቱን ዳግም በማጠናከር በከፋፋዮቹም ሆነ በውጭ ጠላቶቻችን ላይ የበላይ ሆኗል። ይህም አንድነት በሀገራችን ላይ የሚደረጉ ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ አፍራሽ ተግባራትን በመቀልበስ ፤ ተሰሚነታችንን በማጎልበት ከፍ ወዳለ ዲፕሎማሲ ደረጃ እንድንደርስ አስችሎናል።

በነገራችን ላይ ምክር ቤታች ከመንግሥትም ቀድሞ ዲያስፖራው ወደ ሀገሩ እንዲገባና ከሕዝቡ ጎን እንዲሆን ሰፊ የማነሳሳት ስራ ሲሰራ ነበር። ሆኖም ከፖለቲካው ውሳኔ በኋላ ዲያስፖራውን ለማሳመንና በሀገር ላይ እንደማይኮረፍ ለማስረዳት ከባድ ፈተና ገጥሞት ነበር።

በተቻለ ሁኔታ የእኛ ሃፊነት ዲያስፖራውን ማበረታታት በመሆኑ በሀገርና በሕዝብ ላይ ጀርባ መስጠት እንደማይቻል፤ ይህ የጭንቅ ጊዜ እንደሚያልፍ ኢትዮጵያ ግን የማታልፍ በመሆኑ ለሀገራችን ዋጋ የመክፈል ሃላፊነት እንዳለባቸው ማስረዳት ነበር ። ምክር ቤታችን በተለይም ደግሞ ከመንግሥት ጋር በሚያስማሙን ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ድጋፍ አድርጓል።

አዳዲስ ጅምሮች፤ ግኝቶች በሚኖሩበት ወቅት ሁሉ

# ወቅታዊ

መንግሥት የሚሰራቸውን ጥሩ ነገሮች እናበረታታለን። ከመንግሥት ጎን እንቆማለን። በማያስማሙን ጉዳዮች ደግሞ ትግላችንን እንቀጥላለን። መንግሥት በሚሰራቸው ስራዎች ስህተቶቹን እንዲያስተካክል አበክረን እናስገነዝባለን፤ ያንን ደግሞ ተግባራዊ እንዲሆን ተፅዕኖ እናደርጋለን፡፡

ምክንያቱም መደማመጥና መናበብ ካለ በቀላሉ ችግሮችን መቅረፍ የሚያስችሉ እድሎች ይፈጠራሉ። ለዚህም ነው፤ በመንግሥት የተደረገውን ጥሪ አክብረን የተገኘነው። ደግሞ እንዲዚህ አይነት ዝግጅቶች አንድ የተሰበረን ድልድይ ለመጠገን የሚያስችል መሰረት ነው ብለንም እናምናለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ቻይና ህንድ ያሉ ሀገራት ኢኮኖሚያቸውን ያሳደጉት ዲያስፖራዎቻቸው በሚልኩት የውጭ ምንዛሬ ነው። ከዚያ አንፃር የኢትዮጵያ ዲያስፖራዎች እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?**

**አቶ አስባቸው፡-** ትክክለኛ ጥያቄ ነው፤ ምክንያቱም ለአንድ ሀገር እድገት የውጭ ምንዛሬ ወሳኝ ሚና አለው። በዚህ ረገድ የዲያስፖራው ድርሻ ትልቅ ነው። ልክ አንደ ትልቅ ካፒታል ወይም አንድ ትልቅ የነዳጅ ማምረቻ ተቋም የሚቆጠር ነው። ዲያስፖራው ከፍተኛ እውቀት እና አቅም ያለው ቢሆንም ወደ ሀገሩ መጥቶ ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች መኖር አለባቸው፡፡

በተለይ ደግሞ የሀገሪቱ ሰላም አስተማማኝ ካልሆነ ፤ ለንብረቱ ዋስትና የሚሆን ነገር ከሌለ ዲያስፖራው ወደዚህ ለመምጣት አይፈልግም፤ ቢፈልግም የሚጎተትበት ሁኔታ ያጋጥማል። እንደሚታወቀውም ደግሞ ከዚህ ቀደም መንግሥት አምነው የመጡ ዲያስፖራዎች በየተቋሙ ቢሮክራሲ ጫና ምክንያት አብዛኞዎቹ ተዘርፈዋል።

ጥቂት የማይባሉት ኢንቨስት ማድረግ ከጀመሩ በኋላ በተለያዩ ሁኔታዎች የገዙትን መሬት ሳይቀር ተበልተዋል። ፋብሪካዎቻቸውና የተለያዩ ኢንዱስትሪዎቻቸው ሁሉ እንዲወድሙ ተደርገዋል። ይሄንን መንግሥትም ያውቀዋል፤ እኛም ዝርዝራቸውን በተጨባጭም ማቅረብ እንችላለን፡፡

በሌላ በኩል በበርካታ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተንሰራፍቶ ያለው ሙስና ዲያስፖራው በሀገሩ ላይ እንዳያለማ ከሚያደርጉት ቁልፍ ችግሮች መካከል ዋነኛው ነው። በአብዛኞቹ ተቋማት በቀናነት ቀልጣፋ መስተንግዶ ማግኘት የሚቻለው ዲያስፖራው የሚያውቀው ባለሥልጣን ወይም ዘመድ ሲኖረው ነው። አልያ ደግሞ ጉቦ መስጠት ይጠበቅበታል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት ሆኖበታል። በዚህ ምክንያቱ ብዙዎቹ ዲያስፖራዎች ስጋት አለባቸው። ሙስና አሁን ላይ ሀገሪቱ እስትንፋሷን እስከ ማቆም ድረስ አደጋ ላይ አድርሷታል።

ሙስና በዘመናዊ ሁኔታ ተደራጅተው ከላይ እስከታች በሰንሰለት ተያይዘው የሚሰሩበት፤ የጋራ ጥቅም የሚከፋፈሉበት የቡድን ስብስብ ስለሆነ በዚህ ውስጥ ዲያስፖራው በማያውቀው ሁኔታ ውስጥ ለአደጋ ይጋለጣል፤ ገንዘቡንም ያባክናል። ይህ ሁኔታ በመንግሥትና ኢንቨስት በሚያደርጉ ዲያስፖራዎች መካከል ያለው መተማመን የተቀዛቀዘ እንዲሆን አድርጎታል። በአጠቃላይ የሰላም ሁኔታ ከተመቻቸ፤ ሙስናውን በቁርጠኝነት መከላከል ከተቻለ አብዛኛው ዲያስፖራ ሀገሩ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ይፈልጋል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ባሻገር ግን ዲያስፖራው እዚህ ሲመጣ ልክ እንደኖረበት ሀገር የሰለጠነና ቀልጣፋ መስተንግዶ የመጠበቅና ያለውን ችግር ባለመረዳት ቅንጦት የመሰሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ መዋለንዋዩን በሀገሩ ላይ ላለማፍሰስ ሲያቅማማ ይታያል። በዚህ ረገድ የእርስዎ ምልከታ ምንድን ነው?**

**አቶ አስባቸው፡-** እርግጥ ጥያቄያቸው ለዚህ ሀገር ቅንጦት ሊመስል ይችላል፤ ግን ምልከታው እንደተመለካቹ ሁኔታ ይለያያል። በዲያስፖራው በኩል የሚታየው ግልፅነት የተሞላበት አካሄድ ነው። አብዛኞቹ ከኖሩበት ሀገር ባህል አንፃር ፍላጎታቸውን የሚያቀርቡት በቀጥታ ነው። ከመንግሥት አኳያ ማበረታታት የሚገባ ነገር እንዳለ አምናለሁ። ምክንያቱም ዲያስፖራው በስደት ስለኖረ የሚመስለው እንደተገለለ ነው።

መንግሥት ችግር ሲያጋጥመው የዲያስፖራውን ድጋፍ እንደሚሻው ሁሉ ጥሩ ነገሮች ሲኖሩም ሊፈልገው ይገባል። በተለይ ዲያስፖራውን የሚበረታታውም ሆነ ግኑኝነቱን ለማጠናከር የሚሰራው ስራ እምብዛም መሆን



ፎቶ፡-እዮብ ተፈሪ

የለበትም። በመሰረቱ መንግሥት እነዚህን ዲያስፖራው የሚጠይቋቸውን ትንንሽ ጥያቄዎችንም ጭምር የማሟላት ሃላፊነት አለበት። ምክንያቱም 1999 ዓ.ም በወጣው አዋጅ መሰረት የዲያስፖራው መብት ሊከበርለት ይገባል። ደግሞም ከሚያበረክተው አስተዋፅኦ የተወሰኑ እቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ቢያስገባ ምንም ማለት አይደለም። በሌላ በኩል አሁን ላይ ዲያስፖራው በፖለቲካው ውስጥ መሳተፍ ይፈልጋል፤ ለዚህ ደግሞ መንግሥት ሊያሻሽላቸው የሚገቡ መመሪያዎች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ይቅርታ ሳቋርጥዎትና ጥያቄዬ ዕቃ ያስቀረጥ ማስገባት ጋር የተያያዘ ብቻ አይደለም፤ በተለይ ቢሮክራሲው በአንድ ጀምበር እንዲፈታ ከመፈለግና በአሰራሩ ከማማረር ባሻገር ሆድን ሰፋ አድርጎ የመፍትሔ አካል መሆን ለምን አልተቻለም?**

**አቶ አስባቸው፡-** ገብቶኛል፤ ዲያስፖራው በውጭ በሚኖርበት ጊዜ የሚያገኘው መስተንግዶ እዚህ ካለው ጋር የሚገናኝ አይደለም። ምክንያቱም በሰለጠኑት ሀገራት ቀድሞ የተዘረጋ ሥርዓት አለ። ሰው ኖረ፤ አልኖረ፣ መንግሥት ተቀየረ፤ አልተቀየረ የሚያመጣው ነገር የለም። እዛ መነጋገር የሚኖረው ከሲስተም ጋር ነው። እናም ዲያስፖራው በዚያ አስተሳሰቡ ተቀይሯል። ሌላው ይቀርና በአካባቢው አንድ ዛፍ ሊቆረጥ ሲል የመከልከል መብት አለው። ስለዚህ ምንአልባት ዲያስፖራው ከዚያ ተነስቶ ነው ብዙ ጥያቄዎችን የሚያነሳው። የሚኖርበት አካባቢ የሚያደርስበት ተፅዕኖ ነው። ያ ተፅዕኖ በአዕምሮ ውስጥ ይቀረፅና ለምንስ የእኛ ሀገር እንደዚህ አትሰራም? ለምን የእኛስ ባሥልጣኖች እንደዚህ አይሆኑም? የሚል ጥያቄ በቀናነት ሊያነሳ ይችላል።

መጀመሪያ ደረጃ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው ሀገሩ እንድትለወጥለት ከመጓጓትም፤ ከመቆጨትም ስሜት እንደሆነ መረዳት ይገባል። በተጨማሪ ዲያስፖራው ወደ ሀገሩ ሲገባ ያለችው ጊዜ አጭር ናት፤ ምንአልባት ለ15 ቀን ብቻ ይሆናል የመጣው። በነዚህ ጊዜያቶች ውስጥ ጨርሶ ለመሄድ ይጓጓል። ያ ተፈፃሚነት በማይኖርበት ወቅት የግዴታ ችግሮች ይፈጠራሉ። ስለዚህ መደረግ ያለበት ምንድነው? ከተባለ፤ በቅድሚያ የዲያስፖራው ኤጀንሲ የሚባለው ተቋም ከዲያስፖራው ጋር መልካም ግኑኝነት ሊፈጥር ይገባል። ወደዚህ ሀገር ለመምጣ ፍላጎት ያላቸው፤ ኢንቨስት ለማድረግ መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታዎችን፣ አቅጣጫውን የማሳየት፤ በየጊዜው የሚወጣውን የውጭ ፖሊሲ የማስረዳት፤ ያም ወደተግባር እንዲተረጎም ማበረታታት አለበት።

አሁን ክፍተቱ የተፈጠረው ዲያስፖራው ውስጥ ኖረው የማያውቁ ሰዎች ኤጀንሲውን የሚመሩት መሆናቸው ነው። አብዛኞቹ ዲስፖራውን በውል አያውቁትም፤ በሀገሪቱ የተሰጣቸው ፖሊሲና መመሪያ መሰረት ብቻ ነው የሚሰሩት። እንዳተባለው ዲያስፖራው ኩርፊያም፤ የባዛ ራስ ወዳድነትም የሚታይበት ከመንግሥት ጋር ጠንካራና ግልፅ ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ነው። በመሆኑም ኤጀንሲው መጠናከር አለበት፤ ቢቻልም በሚኒስቴር ደረጃ ሊቋቋም የሚችልበትንና ዲያስፖራው ከዚያም አልፎ በምክር ቤት ውስጥ ሊወከል የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጠር ጠቃሚ ነው።

መንግሥት ልክ የፖለቲካ ድርጅቶችን በመንግሥት ደረጃ እንዳወቀረ ሁሉ ነገሮችን ቀለል አድርጎ በማየት ማመቻቸት አለበት። ለምሳሌ ቢጫ ካርድ ቢዘጋጅ ብዙ ነገሮችን ማቅለል ይችላል። እንዲህ አይነት አሰራር በሌሎች ሀገራት የተለመደ ነው። ቢጫ ካርድ ያለው ሰው ለቪዛ አይከፍልም፤ እንደማንኛውም ዜጋ ንብረት ማፍራት ይችላል፤ በሆቴሎች ውስጥ እኩል የመገልገል መብት አለው። እርግጥ መብቱ ገደብ አለው። ሆኖም አሰራሩን ትንሽ ቀላል ማድረግ ቢቻል በተለይ በፖለቲካው ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖረው ቢደረግ የበለጠ የእኔነት ስሜት እንዲኖረው ያደርጋል ባይ ነኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በመንግሥት የተሰጣችሁ እውቅና ሽልማት ብቻ ሳይሆን አደራም ጭምር እንደሆነ ገልፀውልኛል። በቀጣይ ከዲያስፖራው ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**አቶ አስባቸው፡-** በነገራችን ላይ የእውቅና ሥነ-ሥርዓት ምንአልባት ሁሉንም አስደስቷል ማለት አይደለም። ምክንያቱም ለሀገራቸው ለዓመታት የሰሩ ግን ደግሞ በኤምባሲ ደረጃ የማይታወቁ አካላት አልተጋበዙም። እርግጥ በዓለም ያለውን ከሶስት ሚሊዮን በላይ ዲያስፖራ መጋበዝ አይቻልም፤ ግን የመጀመሪያ በመሆኑ ይህንን የዲያስፖራው ህብረተሰብ ሊረዳው ፤ ሊገነዘብ ይገባል። ይሁንና እንደማህበረሰብ የሚደረጉ ስብስቦች ደግሞ የተሰጣቸው እውቅና ምንአልባት እነዚህ አደረጃጀቶች በቀድሞው መንግሥት ጀምሮ በኤምባሲ ጭምር የሚታወቁ አደረጃጀቶች ናቸው።

ከለውጡ በኋላ ደግሞ የግላቸው አደረጃጀት ያላቸው አሉ። ለምሳሌ የእኛ የዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት በኤምባሲዎቻችን ወይም በመንግሥት ተቋም ውስጥ የተደራጀ ድርጅት አይደለም። ግን ደግሞ በአሜሪካ መንግሥት እውቅና ተሰጥቶት ራሱን ችሎ በበጎ አድራጎት ተቋምነት የተቋቋመ ነው። እንደዚህ አይነት እውቅናዎችን ኤምባሲዎች አልሰጡም። እኛ በሀገር ውስጥ ባደረግናቸው የግል ተሳትፎዎችና እንቅስቃሴዎች ትኩረት የሳብን በመሆናችንና እየታወቅን በመምጣታችን ነው ይሄ ጥሪ ሊደርሰን የቻለው እንጂ እንደዲያስፖራ የማህበራት አደረጃጀት ውስጥ ተካተን አይደለም።

አሁን የተሰጠው እውቅና በተለያዩ ሀገራት ያሉት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፤ ቆንስላዎች፤ በራሳቸው ቀደም ሲልም ሆነ አሁን በግብረሃይል ደረጃ ያደራጇቸው እንጂ በውጭ ያሉ ማህበራት የተሳተፉበት አይደለም። ይሄ ደግሞ ቅሬታንም እንዳስነሳ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችም አንብበናል። በሌላ በኩልም ዲያስፖራውን ለመከፋፈል የተደረገ ነው የሚል ቅሬታዎችን ስናዳምጥ ቆይተናል። ያ ግን እንዳልሆነ ለማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ ጠንክሮ መስራት አለበት፡፡

ቆንስላዎቹ የሚፈልጓቸውን ብቻ መርጠው ሳይሆን በንፁህ ህሊና ሁሉንም ማከታት አለባቸው። በመጀመሪ ደረጃ ለሀገር የሚሰሩ የዲያስፖራ ማህበራትን የማበረታት ሃፊነት አለባቸው። ሲስተም ውስጥ እንዲገቡ የመረጃ ቋታቸው ውስጥ እንዲቀመጡ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የእውቅናና የምስጋና ፕሮግራሙ ጥሩ አጋጣሚ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

በተለይ የዲያስፖራ ኤጀንሲ ትኩረት በመስጠት ከቆንስላዎቹ በተጨማሪ ዲያስፖራዎች የሚገናኙበት የራሱ የሆነ ሥርዓት ማበጀት ፤ መድረክ እያዘጋጀ ማወያየት አለበት ፤ እንደዚህ አይነት ተቋማት ካሉ በቀጥታ ለኤጀንሲው እንዲያመለክቱ ቢያደርግ በመመካከር በጋራ ሀገርን ለመርዳት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል።

ከተጠየቀው ጥያቄ አንፃር እንደተግባር ምክርቤታችን እስካሁን ድረስ አቅማችን በፈቀደና በምንችለው መጠን ሰርተናል። መንግሥትም ለዚህ ጥረታችን እውቅናውን ሰጥቶናል። ይህንን ሃላፊነት ተሸክመን ወደመጣንበት ሀገር ስንመለስ አንደኛ በቀጣይ በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ በማቋቋም ረገድ፤ የፈራረሱ ቤቶችን ለመገንባት በሚደረገው ዘመቻ ውስጥ ትልቅ ሚና ይኖረናል ብለን እንገምታለን። ለዚህም እንደበጎ አድራጎት ድርጅት በሀገር ውስጥ ተመዝግበን መንግሥትን እና ሀገርን ለመርዳት እየተንቀሳቀስን ነው።

የምክርቤታችን ስራ አስፈፃሚም ሆነ ቦርድ ሀገርን መልሶ በማቋቋም ረገድ ከመንግሥት ጎን በጋራ በመቆም ኢትዮጵያን አሁን ካለችበት ሁኔታ ማውጣትና ወደ ሰላም የምታደርገውን ጉዞ መደገፍ እና ማበረታታት የሚያስችል ውሳኔ ላይ ደርሷል ።

ለሀገር ሰላም አስፈላጊ መሆኑን፤ በተለይም አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት በቁርኝነት የወሰዳቸውን የሰላም እርምጃዎችን በመደገፍ መግለጫዎችን አውጥተናል፤ ከዚህ አኳያ በቀጣይ በዚህ ጉዳይ በስፋት በመንቀሳቀስ የተሻለ ውጤት እናመጣለን ሚል እምነት አለን ።

የትውልድ ቀረፃን በተመለከተ በተለይም በቅርቡ የሚከበረውን 127ኛ የዓድዋ ድል በዓል ምክንያት በማድረግ በመላው ዓለም እንዲከበር ዝግጅት ጀምረናል። በዚህ ዙሪያ በእንግሊዝ ሀገር ሰፊ ዝግጅት ተደርጓል፤ 250 የምንሆን ኢትዮጵያውያኖች አንድ አይነት ልብስ አሰፍተናል፤ ኢትዮጵያን አጉልቶ ሊያሳይ የሚችል፤ የዓድዋን ክብረበዓል በሚመጥን ሁኔታ የድል በዓሉን ልናጎላና ልናሳይ እየተንቀሳቀስን ነው።

በዓሉ ታሪካዊ ቅርሳችን መሆኑን ለመላው ዓለም ለማሳየት ትልቅ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ሰረገላም ተከራይተናል፤ አንድ ሺ የሚሆን ሰው «የንጉሥ እራት» በሚል ግብዣ ተጠርቷል። አሜሪካ፤ ካናዳ፤ በአፍሪካ ተመሳሳይ ፕሮግራም ይኖረናል። ዓድዋ ዘመን ተሻጋሪ የኢትዮጵያ ቅርስ ሆኖ እንዲከበር በተለይም በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ በከፍተኛ ሁኔታ እየሰራን ነው።

በሀገር ውስጥም ቢሆን ዓድዋ የመበሻሸቂያ መድረክ መሆን የለበትም ብለን ስለምናምን ሥርዓት ባለውና የዓድዋን ክብር በሚመጥን መልኩ እንዲዘጋጅ የተበታተኑትን ወጣቶች፤ ጥንታዊ አርበኞችንም በጋራ በማድረግ በጤናማ ሁኔታ እንዲከበር ፤ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቅርስ እንዲሆን፤ ትውልድም ደግሞ ከዚያ መማር የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ለማመቻቸት እየሰራን ነው።

የሀገርን ሉዓላዊነት ለመጠበቅ አንድነት ፤ ፍቅር፤ የጋራ መተሳሰብ፤ የጋራ መረዳዳት እንዲኖር የሚያደርጉ ስራዎችን በወጣቱ ላይ በመስራት ዝግጅት እያደረግን ነው። ደብረብርሃን፤ ጎንደር ፤ አርባምንጭ ፤ ሐረር ፤ አዲስ አበባ ላይ ትልልቅ ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ። በዓለም ታሪክ ውስጥ ረጅሙ የጎዳና ትርኢት በሚቀጥለው ሁለት ዓመት ውስጥ ይካሄዳል። ይህም በጊነስ ቡክም ለማስመዝገብ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

ይህም ደግሞ የዓለምን ቱሪዝም ወደኢትዮጵያ በማምጣት የምንችልበት ሁኔታ በተለይም ዓድዋ የመላው ጥቁር ሕዝብ ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ ዓለምን ነፃ ሊያደርግ የሚችል፤ የመፍትሔ ሃሳብ የወለደ፤ ኢትዮጵያውያኖችን ብቻ ሳይሆን በባርነት ስር አንገታቸውን የደፉ፤ ጥቁሩንም ነጩንም ጭቁን ሕዝብ የመፍትሔ ሃሳብ ሆኖ የተፈጠረ ነው።

ከዚህ አንጻር ዓድዋን እንደአንድ ትልቅ በዓል አድርገን ስለምናስበው ዓለም አቀፍ የዓድዋ ዘካሪያን ማህበርን እያቋቋምን ነው። ይሄ በጣም ጥሩ ጅማሬ ነው። ወደፊት የምንሰራቸው ትልልቅ የሆኑ ፕሮጀክቶች አሉን። ፕሮጀክቶቻችንን ከቱሪዝም ዘርፉ ጋር ተናበው የሚሰሩ ናቸው ፤ ሁለቱን አቀናጅቶ ለመሄድም የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት እየሰራ ይገኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ አስባቸው፡-**እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ



## ኔቶ ሩሲያ የኒውክለር ስምምነቱን እንድታከብር አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኔቶ፣ ሩሲያ ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር የፈረመችውን ቀሪውንና የመጨረሻውን የኒውክለር ቁጥጥር ሥምምነት እያከበረች አለመሆኗ ያሳሰበው መሆኑን አስታወቀ።

የሩሲያውን የዩክሬን ወረራ ተከትሎ ውጥረት እየተባባሰ ባለበት ሰዓት፣ የኔቶ ኃይሎች መሪ የሆነችው ዩናይትድ ስቴትስ፣ ሞስኮ አስርት ዓመታትን ያስቆጠረውን "የኒው ስታርት ፓክት" ወይም የአዲስ ጅማሮ ሥምምነትን አስመልክቶ የገባቸውን ቃል አልጠበቀችም ስትል ከሳለች።

ባለፈው ማክሰኞ፣ ዋሽንግተን፣ ሩሲያ በሥምምነቱ መሠረት የተገባውን ቁጥጥር እና በጉዳዩ ዙሪያ የሚደረገውን ንግግር መሰረዟን አውግዛለች ሲል አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

ይሁን እንጂ የቀዝቃዛው ጦርነት ባላንጣዋ የኒውክለር ጦር መሣሪያዎቿን ከተደረሰበት ሥምምነት ውጪ እያስፋፋች ነው ስትል አልከሰሰችም።

"የኔቶ አጋሮች የአዲስ ጅማሮ ሥምምነት የሩሲያና ዩናይትድ ስቴትስን የኒውክለር ስትራቴጂ ኃይሎች በመገደብ ለዓለም አቀፍ መረጋጋት አስተዋጽኦ ማድረጉን ይስማማሉ" ሲሉ 30 የህብረቱ ጠንካራ አባላት ባወጡት የጋራ መግለጫቸው ማስታወቃቸውን አሶሼትድ ፕሬስ አስነብቧል።

"ስለሆነም ሩሲያ በህግ አሳሪ የሆነውን የአዲስ ጅማሮ ሥምምነትን ማክበር አለመቻሏን በስጋት ተገንዝበናል" ያለው የአባላቱ መግለጫ "ሩሲያ ግዴታዎቿን በመወጣት ተቆጣጣሪዎቹ እንዲመለሱና ንግግሩም እንዲጀመር እንድትፈቅድ ጥሪያችንን እናቀርባለን" ብሏል።

ሩሲያ በበኩሏ ዋሽንግተን በሁለቱ አገሮች መካከል የነበረውን የመሣሪያ ቁጥጥር ሰርዛለች ስትል ትከሳለች።

ሞስኮ ባለፈው ነሐሴ ወር መግቢያ ላይ፣ የአዲስ ጅማሮ ስምምነትን በመጣስ ዩናይትድ ስቴትስ ተቆጣጣሪዎች የጦር ሰፈሮቿን እንዳይመረምሩ አዛለች።

ለዚህም የሰጠችው ምክንያት ዋሽንግተን በተመሳሳይ መደረግ የነበረበትን የሩሲያ ተቆጣጣሪዎችን አግዳለች በሚል ነበር ሲል የዘገበው አሶሼትድ ፕሬስ፣ ዋሽንግተን የሩሲያን ክስ ማስተባበሏን ዘግቧል።

## የቀድሞ የፓኪስታን ፕሬዚዳንት ፐርቬዝ ሙሻራፍ በ79 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ



ሙሻራፍ በተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች ዱባይ በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ነው የእረፍታቸው ዜና ዛሬ የተሰማው።

ሙሻራፍ ባለ አራት ኮከብ ጄኔራል የነበሩ ሲሆን ደም ባላፋሰሰ መፈንቅለ መንግሥት እንደ አውሮፓውያኑ በ1999 ሥልጣን ከያዙ በኋላ 10 ዓመት ለሚጠጋ ዘመን ፓኪስታንን መርተዋል።

ጀኔራል ሙሻራፍ በወታደሩ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው፣ ሰልፍ አሳማሪ፣ ከእነ በትረ መኮንናቸው ወታደራዊ አለባበስ የሚያውቁ፣ ጥንቁቅ እና ንቁ ጄኔራል ነበሩ ይባልላቸዋል።

በአገራቸው ሕዝብ ዘንድ ጥርስ ውስጥ ያስገባቸው ደግሞ አሜሪካ መራሹን የጸረ ኢስላማዊ አክራሪዎችን ዘመቻም ተቀብለው በማስፈጸማቸው ነበር።

ሙሻራፍ እምብዛምም ባልተለመደና የሰውነት ክፍሎችን በሚጎዳ አሚሎይዶሲስ በሚባል በሽታ ሲሰቃዩ ነበር። ለረዥም ጊዜም የአልጋ ቁራኛ የነበሩ ሲሆን በተሽከርካሪ ወንበር (ዊልቼር) ነበር የሚንቀሳቀሱት።

የፓኪስታን መከላከያ ሚኒስትር በመገናኛ ብዙኃን ባስተላለፈው አጭር መልዕክት ለሙሻራፍ አላህ ምሕረቱን ይስጣቸው፤ ለቤተሰባቸውም መጽናናትን እንመኛለን ብሏል።

ሙሻራፍ የቀድሞ የኮማንዶ አባል ሲሆኑ የተሳካ የሚባል መፈንቅለ መንግሥት ከመሩ በኋላ ፓኪስታንን በአስቸጋሪ ወቅት የመሩ ፖለቲከኛ ናቸው።

ፓኪስታን ከሕንድ በ1947 ከተለየች በኋላ በርካታ መፈንቅለ መንግሥት አስተናግዳለች። ሙሻራፍ የገለበጡት የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ናዋዝ ሽሪፍን ነበር።

ኒኩሌር ታጣቂዋን ፓኪስታንን በከፍተኛ ውዝግብ የመሩት ሙሻራፍ ከሕንድ ጋር ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ የገቡበት ወቅትም ነበር። በመጨረሻም በ2008 ከሥልጣን የወረዱት ክስ ከተመሰረተባቸው በኋላ ነው።

ሙሻራፍ አገራቸው በአሸባሪዎችና አክራሪዎች በምትናጥበት ወቅት አገራቸውን ያገለገሉ መሪ ሲሆኑ ከበርካታ የግድያ ሙከራዎችም አምልጠዋል።

የሙሻራፍ ፓርቲ ከ2010 ጀምሮ በምርጫ ቢወዳደርም የተሳካለት አልሆነም። ሙሻራፍ በ2019 በሌሉበት የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው የነበረ ሲሆን ከወር በኋላ ይህ ፍርድ ተቀልብሷል።

በመጨረሻም የአገር ክህደት ክስ ከተመሰረተባቸው በኋላ በስደት ወደ ዩናይትድ አረብ ኢምሬትስ በማቅናት በዚያው ሕይወታቸው አልፏል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች በመልሶ ግንባታው

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ባለፉት ሁለት ዓመታት በአገራችን በነበረው አለመረጋጋት በርካታ መሰረተ ልማቶች እና የሕዝብ መገልገያ ተቋማት መውደማቸው የሚታወስ ነው። ከነዚህ የህዝብ መገልገያ ተቋማት መካከል ትምህርት ቤቶች በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። ትምህርት ቤቶች አገር እንድትደርስ ለሚታለምላት የሥልጣኔም ሆነ የእድገት ደረጃ እውን መሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ። ከነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚወጡ ዜጎች ለዚህ ህልም መሳካት ዋነኞቹ ተዋንያን ናቸው። እነዚህን ለአገር እድገትና ብልፅግና የላቀ ሚና የሚጫወቱ ዜጎች ለማፍራት ጥራታቸውን የጠበቁና ምቹ ከባቢን የሚፈጥሩ ትምህርት ቤቶች መገንባት ያስፈልጋል።

በእውቀት ያልተገነባና ምክንያታዊነትን ያልተላበሰ አእምሮ ከሌሎች መግባባት ይቸግረዋል አለፍ ሲልም አገር ሊጎዳ የሚችል ጠንቅ ይሆናል። የዛሬ ችግሮቻችንም ከዚህ እውነት የሚመዘዙ እንደሆኑ ማስተዋል አያዳግትም፡፤ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን ከሁሉ በፊት ትምህርት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል።

ይህን በመረዳት ትምህርት ሚኒስቴር ሀሙስ ጥር 25/2015 ዓ.ም በጦርነት ሙሉ ለሙሉ የወደሙ እና በልዩ የዲዛይን ሞዴሎች የሚገነቡ 71 ትምህርት ቤቶችን የመልሶ ግንባታ ስራ በይፋ አስጀምረዋል። የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በይፋዊ የስራ ማስጀመሪያ መርሀግብር ላይ እንደገለጹት፤ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ትምህርት ቤቶቹ በተሻለ ዲዛይን የሚጠበቅባቸውን መሠረተ ልማት አሟልተው ይገነባሉ።

ምቹና የተሻሉ ትምህርት ቤቶችን መገንባት ለትምህርት ጥራት ወሳኝ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ አዲስ የሚገነቡት ትምህርት ቤቶች ከኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር ጋር በተፈፀመው የመግባቢያ ሰነድ መሰረት ደረጃቸውን የጠበቁና ለመማር ማስተማሩ ምቹ የሆኑ የትምህርት ቤት ሞዴሎች የዲዛይን ስራ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቋል። ከዚህ በኋላ የሚገነቡ ትምህርት ቤቶች በነዚህ ሞዴሎች መሰረት የሚገነቡ ይሆናሉ፡፡

በጦርነቱ ሙሉ ለሙሉ የወደሙ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት የሚያስችል ሁለት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ለማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ዙር ከሚገነቡ 71 ትምህርት ቤቶች መካከል 45 ትምህርት ቤቶች በአማራ ክልል፤ አምስት ትምህርት ቤቶች በአፋር ክልል በድምሩ 50 ትምህርት ቤቶች ትምህርት ሚኒስቴር ከዓለም ባንክ ባገኘው ድጋፍ የሚገነባቸው ይሆናሉ። ሁለት ትምህርት ቤቶች በአፋር ክልል ሶስት ትምህርት ቤቶች ባጠቃላይ አምስት ትምህርት ቤቶች በዲያስፖራ ትረስት ፈንድ እንደሚገነቡ በመርሃግብሩ ተገልጿል። ቀሪዎቹ ስምንት ትምህርት ቤቶች በአፋር ክልል፣ ሶስት ትምህርት ቤቶች በአማራ ክልል እንዲሁም አምስት ትምህርት ቤቶች በተለያዩ ክልሎች በሰዎች ለሰዎች ድርጅት ይገነባሉ፡፡





በአማራና በአፋር ክልሎች 71 ሙሉ ለሙሉ በጦርነቱ የወደሙ ትምህርት ቤቶች በዚህ ዓመት ግንባታቸው የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ ተብሎ ይጠበቃል። ለዚህም 55 የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ተመርጠው ወደ ሥራ እንደገቡ ይፋ ተደርጓል። የግንባታ ግብዓት ለግንባታው መጓተት እንቅፋት እንዳይሆን ትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊነቱን ወስዶ ሲሚንቶ ከአራት ድርጅቶች በመግዛት ላይ ይገኛል፡፡

በሁለቱ ክልሎች ሙሉ ለሙሉ የወደሙ 71 ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመገንባት 55 የግንባታ አማካሪዎችና ኮንትራክተሮች ወደ ሥራ እንደገቡ ይፋ በተደረገበት መድረክ ላይ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደሚናገሩት፤ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ግንባታቸው በዚህ ዓመት የሚጠናቀቁ ይሆናል። ለ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ሁሉም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መቀበል ይጀምራሉ። ስለሆነም ትምህርት ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን አገር አምኖባቸው የመረጣቸው ሥራ ተቋራጮች ኃላፊነታቸውን በሚገባ በመወጣት ካለምንም ማጭበርበርና የጥራት ማጓደል ስራቸውን በአግባቡ ሰርተው ማስረከብ ይኖርባቸዋል። ስራቸው በንግግር ሳይሆን በተግባር የሚታይ መሆን ይኖርበታል፤ ትምህርት ቤቶቹን ገንብቶ ለመጨረስ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ቀድሞ ተጠንቶ የተጠናቀቀ በመሆኑ በተመደበላቸው የገንዘብ መጠን ሰርተው ማጠናቀቅ ይገባቸዋል ሲሉ ይናገራሉ።

ትምህርት ሚኒስቴር በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ትምህርት ቤቶች በደረሰባቸው የጉዳት መጠን በሶስት ከፍሎ የተመለከቷቸዋል። እነዚህም ሙሉ ለሙሉ የወደሙ፣ በከፊል የወደሙ እና መማሪያ ክፍሎች ላይ ጉዳት ያልደረሰባቸው ነገር ግን የተለያዩ ቁሳቁሶቻቸው የተዘረፉ ናቸው። በከፊል የወደሙ እና መማሪያ ክፍሎች ላይ ጉዳት ያልደረሰባቸው ነገር ግን የተለያዩ ቁሳቁሶቻቸው የተዘረፉ ትምህርት ቤቶች በክልል መንግሥታት የሚገነቡ ሲሆኑ ሙሉ ለሙሉ የወደሙ ሶስት ሺ 300 ትምህርት ቤቶች በትምህርት ሚኒስቴር የሚገነቡ ይሆናል።

በጦርነቱ ወቅት ሙሉ ለሙሉ ከወደሙ አጠቃላይ ሶስት ሺ 300 ትምህርት ቤቶች መካከል አንድ ሺህ 65 ትምህርት ቤቶች በአማራ ክልል ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፤ 95 የሚሆኑት ደግሞ አፋር ክልል የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ናቸው።

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ጥራትን ለመጨመርና ወደፊት አገር የሚመሩ ዜጎች ለማፍራት ጥራታቸውን የጠበቁና ምቹ ትምህርት ቤቶችን መገንባት አስፈላጊ ነው ብሎ በማመን አስራ ሶስት የአዳሪ ትምህርት ቤቶችን እንዲሁም 50 ሞዴል ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ፕሮጀክት ቀርፆ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

# ስፖርት



## የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሸናፊነት ተጠናቀቀ

አስማየሁ ግዛው

11ኛው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና በአሰላ አረንጓዴው ስቴድየም ሲካሄድ ቆይቶ ትናንት ተጠናቋል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም አጠቃላይ የቻምፒዮናው አሸናፊ በመሆን የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል።

በሴቶች መካከል የተካሄደውን ውድድር ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አጠቃላይ አሸናፊ በመሆን ያጠናቀቀ ሲሆን በወንዶች ደግሞ ሦስተኛ ሆኖ ጨርሷል። ይህም አጠቃላይ ውድድሩን በነጥብ ቀዳሚ ሆኖ እንዲያጠናቅቅ አድርጎታል። በወንዶች ሁለተኛ ሆኖ ያጠናቀቀው ጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ ማእከል በአጠቃላይ በሰበሰበው ነጥብ ሁለተኛ በመሆን ውድድሩን ፈጽሟል። ኦሮሚያ ክልል በበኩሉ በሁለቱም ጾታ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀ ሲሆን እንደ አጠቃላይ ሦስተኛ ደረጃን ይዞ ውድድሩን ጨርሷል።

ቻምፒዮናው ባለፉት ሁለት ቀናት በተለያዩ የውድድር ዓይነቶች ጠንካራ ፉክክሮችን ያስተናገደ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል በአራት በአራት መቶ ድብልቅ ሪሌይ (የዱላ ቅብብል) ከፉተኛ ፉክክር በማሳየት ጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ ማእከል አንደኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል። ኦሮሚያ ክልል ሁለተኛ በመሆን የብር ሜዳለያውን ወስዷል። ሦስተኛና የነሐስ ሜዳለያ ተሸላሚው ደግሞ ኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ መሆን ችሏል።

ሌላው የተመልካችን ትኩረት የሳበውና ተወዳዳሪዎች በእጅጉ የተፎካከሩበት የወንዶች ከፍታ ዝላይ ውድድር ሲሆን፣ አኬሎ ኡጁሉ ከኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ አሸናፊ ሆኗል። ኡጁሉ አንበሴ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ በተመሳሳይ ሁለት ሜትር ከፍታን የዘለለ ሲሆን፣ ገመዳ አባተ ከጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ ሦስተኛ ሆኖ አጠናቋል። በውድድሩ ተመሳሳይ ከፍታ መዝለል የቻለው ኡጁሉ አንበሴ ለአዲስ ዘመን በሰጠው አስተያየት፣ ዝግጅቱ ጥሩ እንደነበረና ውድድሩ ፈታኝ እንደሆነ ተናግሯል። ክለቡ ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት ጥሩ ቢሆንም የመለማመጃ መሣሪያ እጥረት እንዳለም አልሸሸገም። አትሌት ኡጁሉ ለሉሳካው ውድድር ጠንክሮ እንደሚሠራና ለአገሩም ወርቅ እንደሚያስመዘግብ ጨምሮ ገልጿል። አኬሎ ኡጁሉ በበኩሉ «መጀመሪያ ስገባ ፈርቼ ነበር ግን ብዙ የሚያበረታታ ደጋፊ በመኖሩ አንደኛ ልወጣ ችያለሁ» ሲል ገልጿል። አትሌት ኦኬሎ በአካዳሚው ስልጠና በሳምንት ሦስቴ እንደሚያደርግ ገልጾ ስፖርቱ የሚፈልገው ቁሳቁስ እጥረት ቢቀረፍ የተሻለ ውጤት እንደሚመዘገብ አስተያየቱን ሰጥቷል።



ቻምፒዮናው በተለያዩ ውድድሮች ጠንካራ ፉክክር አስተናግዶ ትናንት ተጠናቋል፣

ውድድሩ ትናንት ፍፃሜ ሲያገኝ በሁለቱም ጾታ የተካሄደ የ10ኪሎ ሜትር እርምጃ ውድድር ማለዳ ላይ ተካሂዷል። በዚህም በሴቶች አባቡ አያሌ ከመቻል 52:30:20 በሆነ ሰዓት በቀዳሚነት ስታጠናቅቅ፣ ብርሃን ሙሉ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ56:42:05 ሁለተኛ ሆና አጠናቃለች። አልማዝ እሸቱ ደግሞ ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች በ58:55:89 ሰዓት ሦስተኛ ሆና ጨርሳለች። በወንዶች ምስጋና ዋቁማ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 42:37:91 በሆነ ሰዓት አንደኛ ሆኖ ጨርሷል፣ እሱን ተከትሎ መለስ ሙሉ ከአማራ ክልል 42:48:81 በሆነ ሰዓት መግባት ችሏል። የሦስተኝነቱን ቦታ ደግሞ ፍቃዱ ጥላሁን ከአማራ ፖሊስ በ43:06:10 በሆነ ሰዓት ይዟል።

የወንዶች 5 ሺ ሜትር ከፍተኛ የሆነና በአስሩም ዙሮች ሁሉም ተወዳዳሪዎች እልህ አስጨራሽ ፉክክርን ያደረጉበት ነው። ውድድሩን ከፍተኛ ትንቅንቅ በማድረግ ንብረት ክንዴ ከጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ 14:26:45 በመግባት የወርቅ ሜዳሊያውን ሲወስድ ፣ መንግስቱ አማረ ከአማራ ክልል 14:26:94 ሁለተኛ ሆኖ አጠናቋል። ይበልጣል ጋሻው ከአማራ ማረሚያ 14:27:95 በመግባት ሦስተኛ ደረጃን መያዝ ችሏል።

በወንዶች የጦር ውርወራም ከፍተኛ ፉክክርና የተደረገ ሲሆን ሳሙኤል ደበላ ከኦሮሚያ ክልል 70.78 ሜትር በመወርወር አንደኛ መሆን ችሏል። ታደሰ ሂርቦዬ ከኦሮሚያ ክልል 68.68 ሜትር በመወርወር ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ሲያጠናቅቅ፣ አኮት ጀምስ ከጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ ሦስተኛ በመሆን ጨርሷል። ቻምፒዮናው በቆየባቸው ስድስት ተከታታይ ቀናት በተለያዩ ርቀቶችና የሜዳ ላይ ተግባራት ውድድሮች ጠንካራ ፉክክሮችን ሲያስመለክት መቆየት ችሏል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተሳትፎና ውድድር ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ የውድድሩን መጠናቀቅ አስመልክቶ ለአዲስ ዘመን በሰጡት አስተያየት፣ ከዕድሜ ተገቢነት ክፍተት ውጪ ቻምፒዮናው በጥሩ ሁኔታ እንደተፈጸመ ተናግረዋል። ጥሩ ተፎካካሪዎችና አዳዲስ አትሌቶችም የታዩበት መሆኑንም አክለዋል። አላማውም ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶችን ለመምረጥ መሆኑን የገለጹ ሲሆን፣ በዕድሜ ተገቢነት የተቀነሱ አትሌቶች ውሳኔውን በጸጋ መቀበላቸው መልካምና ወደፊትም መቀጠል እንዳለበት አስረድተዋል።

አጠቃላይ ውድድሩን በሦስተኝነት የጨረሰው የኦሮሚያ ክልል አትሌት የሆነውና የጦር ውርወራን ያሸነፈው ሳሙኤል ደበላ ውድድሩ ቆንጆ መሆኑን ተናግሮ ከዕድሜ ተገቢነት ጋር ተያይዞ በፌዴሬሽኑ የተወሰደው እርምጃ በደንብ ሊታይ እንደሚገባ አስረድቷል። አትሌት ሳሙኤል የተወሰደው እርምጃ ሁሉንም ያማከለና ለሁሉም የሚያሳምን ሊሆን ይገባል ሲልም ገልጿል።


# Invitation for Bid

**BID No. DDAEU/NCB/003/15**

Dire Dawa Administration Electric Utility invites sealed bids from eligible bidders by this National Competitive Bidding (NCB) for the procurement of Construction of Service Block and Customer Waiting, Parking and Site Work in open bidding procedure.

| SR. No. | Description of goods | Bid Security ETB | Bid Closing date & time | Bid Opening date & time |
|---|---|---|---|---|
| 1 | For Supply and fix ALUMINUM PARTITION WALL WITH DOOR AND STEEL STRUCTURE WORK at Dire Dawa Administration Customer Service Center #1 | ETB. 36,500.00 | February 23, 2023, 3:00PM | February 23, 2023,3:30PM |

1. The Dire Dawa Administration Electric Utility invites sealed bids from eligible Bidders who have GC/BC-5 & Above, Construction Licenses valid for the current Ethiopian Fiscal Year, (EFY, 2015), Trade License valid for the current Ethiopian Fiscal Year (EFY, 2015). VAT Registration Certificate, TIN Certificate, valid Tax Clearance Certificate and with Registration in the Suppliers List of Public Procurement and Property Administration Agency (PPPAA). The bidders by providing all necessary Materials. Equipment and Labor which is proposed to be built at the mentioned sites.
2. Bidding will be conducted in accordance with the OPEN Bid Tendering Procedures contained in the Public Procurement Proclamation of the Federal Government of Ethiopia. Bidders who participate must have similar experience to the proposed Works.
3. Interested eligible bidders may obtain further information and clarification from Dire Dawa Administration Electric Utility (DDAEU) and inspect the bidding documents at the address given below.

**Dire Dawa Administration Electric Utility (DDAEU)**
**Procurement, Logistics, Warehousing & Facility Office**
**Greek Camp Behind Dire Dawa stadium**
**Dire Dawa, Ethiopia**
**Tel. +25-211-00-23/25-112-98-45**
**Website: www.eeu.gov.et**

4. A complete set of bidding Documents may be purchased by any interested eligible bidders at Piassa, Degoule square Electric Utility Hade Quarter Building 3rd floor and Greek Camp, Behind Dire Dawa stadium Dire Dawa Administration Electric Utility office and upon payment of non-refundable fee of against payment receipt of ETB. 800.00 (Eight hundred Birr).
5. Bids must be delivered on or before the closing date and time to the above mentioned address. All bids must be accompanied by a bid security in the form of (CPO or Unconditional Bank Guarantee) as mentioned above. Late bids shall be rejected and will be returned unopened to the Bidder.
6. The Bid is Single Stage Single envelope system; Technical offer, Financial & Bid Security will be opened in the presence of the bidders or bidders representatives' who choose to attend at the address above on the above mentioned date and time.
7.Bidders are advised to submit their offer after examining the bid document carefully.
8. Dire Dawa Administration Electric Utility (DDAEU) reserves the right to reject all or partial bid without assigning any reason thereof Bidders are instructed to fill; sign and sealed all the forms of the bid documents.

All Bids must include value added tax (VAT) on the summary of the bid price Partial rebate, like fixed sum and rebate on some items is not acceptable.

**Dire Dawa Administration Electric Utility**

**ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ**
**ጨረታ ቁጥር ድ/አ/ኤ/አ/ግ/ጨ/002/2015**
**(ሎት 1- ሎት 2)**

የድሬዳዋ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት በስሩ ለሚገኙ ሰራተኞች የሥራ ክፍሎች እና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የሚውሉ የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የተለያዩ ዓይነት ዕቃዎችን በዘርፉ ከተሰማሩ ድርጅቶች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| ሎት | የእቃው ዓይነት | የመዝጊያ ቀን እና ሰዓት | የጨረታ መከፈቻ ቀን እና ሰዓት | የጨረታ ዋስትና መስከበሪያ |
|---|---|---|---|---|
| ሎት-1 | የሴፍቲ ዕቃዎች (Safety Tools) | የካቲት 16 ቀን 2015 ዓ.ም 9:00 | የካቲት 16 ቀን 2015 ዓ.ም 9:30 | ብር 27,000.00 (ሃያ ሰባት ሺህ) |
| ሎት-2 | Air condition, 4K Television, / Outdoor LED Display Board & Customer Wireless Queue system | | | ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) |

1. ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የተጨ.እ.ታ፣ የግብር ከፋይ መ/ቁጥር እና ገቢዎች ባለስልጣን ጽ/ት ጨረታ ላይ እንዲሳተፉ የሚል ማስረጃ ያለው በጨረታው መሳተፍ ይችላል፡፡
2. ተጫራቾች የመንግስት ድርጅቶች በሚያወጡት ጨረታ ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ በግዥ ኤጀንሲ ድህረ-ገጽ ላይ የተመዘገቡ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. በዚህ ጨረታ ለመሳተፍ ከላይ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች በማያያዝ መወዳደር የሚችሉ ሲሆን፤ ዝርዝር ሁኔታው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ይገኛል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ማስታወያው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት ፒያሳ ደጎል አደባባይ አጠገብ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና መ/ቤት ፕሮኩዩርመንት እና ፋሲሊቲ ቢሮ እና ግሪክ ካገኘ ድሬዳዋ ስታዲየም አጠገብ በሚገኘው የድሬዳዋ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ግዥ፣ ሎጀስቲክስ፣ ዌርሀውስ እና ፋሲሊቲ ቢሮ ቁጥር 04 ቢሮ የማይመለስ ብር 600.00 (ስድስት መቶ) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች ለጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ የሚያቀርቡት የገንዘብ መጠን ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ሆኖ ለባንክ በተረጋገጠ ቼክ(CPO) ወይም በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ለስድስት ወራት የሚያገለግል የባንክ ዋስትና (Bid Bond) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ቴክኒካል ኦሪጅናል እና ኮፒ » እና ፋይናንሻል ኦሪጅናል እና ኮፒ » በማለት በተለያየ ፖስታ በማሸግ እና ሁለቱን በአንድ ትልቅ ፖስታ በማድረግ ጨረታ ቁጥር ድ/አ/ኤ/አ///ጨ/002/2015 ከሎት-1 እና ሎት-2 የሚል ምልክት በማድረግ እስከ የካቲት 16 ቀን 2015 ዓም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ግሪክ ካንፕ ድሬዳዋ ስታዲየም አጠገብ በሚገኘው የድሬዳዋ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ግዥ፣ ሎጀስቲክስ ዌርሀውስ እና ፋሲሊቲ ቢሮ ቁጥር 04 ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት የሚኖርባቸው ሲሆን ጨረታው በተመሳሳይ ቀን ከቀኑ 9፡30 ሰዓት የሚከፈት ይሆናል፡፡
7. የጨረታው ከላይ በተገለፀው መሠረት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
8. ተጫራቾች ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር +025-211-00-23/025-112-98-45 መደወል ይችላሉ፡፡
9. ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት**